# ያማርኛ መደብ፣ ጾትና ቁጥር አመልካች ምዕላዶችን ማስተማሪያ አንድ ስልት

**አብርሃም ጎዝጉዜ ግዛው**

**አማርኛን በማስተማር ሥነ-ዘዴ ለማስተርስ**

ዲግሪ ማሟያ፣ለአዲስ አበባ ዩንቨርስቲ

የቀረበ ቲሲስ

አዲስ አበባ

1987 ዓ.ም

አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ
ድኅረ ምረቃ ትምህርት ቤት

# የአማርኛ መደብ፣ ጾታና ቁጥር አመልካች ቅጥያ ምዕላዶችን ማስተማሪያ አንዱ ስልት

በ


አብርሃም ገዝገዝ ገዛው
ቋንቋዎች ጥናት ተቋም


የፈታኞች ማረጋገጫ፣

______________________ ______________________
አማካሪ

______________________ ______________________
ፈታኝ

______________________ ______________________
ፈታኝ

______________________ ______________________
ፈታኝ

## ምስጋና

የናውና እጅግ ከፍተኛው ምስጋናዬ ለማከሪዬ ለዶ/ር ደጀኔ ለታ ይሁንልኝ። ለዚህ ጥናት ከበረከቱልኝ ከፍተኛ ሙያዊ ድጋፍ በሻገር፣ ትምህርቴን ለማቋረጥ በንገራገርኩበት ወቅት በግል መከረውና በሚቀርቡኝ ሰዎች አስመከረው ለዚህ ያበቁኝ በመሆናቸው በለውለተኛ አባቴ ናቸው። ወደር የማይገኝለትን ትሁት ሰብእናቸውንም ምንጊዜም አልረሰውም።

ቀጥሎ ከልቤ ማመስገን የምፈልገው ምክርና ቅን ሀሳባቸው እስከ ዛሬ ያልተለየኝን የቀድሞው አማከሪዬን አቶ ፍስሓ ሲሳይን፣ የትምህርት እድል እንዳገኝ ድጋፍ የሰጡኝን ዶ/ር አረጋ ኃይለሚካኤልንና ዶ/ር አምሳሉ አክሊሉን፣ በዚህ ርዕስ ላይ እንድሰራ የረዱኝን የሥነ-ልሳን መምህሬን ዶ/ር በዩ ይማምን፣ በምጠይቃቸው ሁሉ መልካም ትብብር ያደርጉልኝን የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ-ጽሑፍ ክፍል ሊቀመንበር የሆኑትን አቶ ዘሪሁን አስፋውንና አቶ ይልማ ከበደን እንዲሁም የልብ ወዳጄን አቶ አወል አህመድ ሸሚልን ይሆናል። ለነዚህ ሰዎች በውነት ከፍ ያለ ለመዘርዘር ቃላት የለኝ።

በመጨረሻ ምስጋና የሚገባቸው የገንዘብ ድጋፍ ያደረጉልኝ፣ ወንድሞቼ አቶ ወንድወሰን [illegible] አቶ ለማ አሰፋ፣ ትምህርት ቤት ጊዜ ጓደኞቼ አቶ [illegible]፣ [illegible] አቶ ደርጋሽና [illegible]፣ የሥራ ባልደረባዬ መምህር አመኑ አሰፋና ጽሑፉን የተየቡልኝ ወ/ሮ ፍቅሬ ገመቹ ናቸው።

## አጠቃሎ (Abstract)

በቀለማዊው ያማርኛ አፃፃፍ ሳቢያ የ2ኛ ደረጃ ተማሪዎች ያማርኛ ቅጥያ ምእላዶችን ለይቶ የመረዳት ችግር ያለባቸው መሆኑን በጽንአት የሚያነሳው ይህ ጥናት ችግሩ በባለሙያዎች ታውቆና ትኩረት ተሰጥቶት ያማርኛ ምእላዶች ማስተማሪያ ብልሃት እንዲመነጭ ያሳስባል። ለዚህ ግብ በር ከፋች የሚሆን በይነቱ አዲስ የሆነ አንድ ስልትም ያቀርባል።

ሦስት ህግጋት ያሉት ይህ ስልት ያማርኛ መደብ፣ ጾትና ቁጥር አመልካች የሆኑ ቅጥያ ምእላዶችን ከቃል ላይ ለይቶ ለማግኘት ያስችላል። ከፊል ፍትነታዊ በሆነ ያጠናን ዘዴ፣ በ73 የ10ኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ በተደረገ ጥናት ተማሪዎቹ ከቃል ላይ በግልጽ ሊታዩ የማይችሉ ቅጥያ ምእላዶችን ለይቶ የመረዳት ችግራቸው የጎላ መሆኑ ሲረጋገጥ፣ በመፍትሔነት የቀረበው ስልትም ከፍተኛ ጠቀሜታ ያለው መሆኑ ታይቷል። ጥናቱ እግረ መንገዱን ያማርኛ መደብ፣ ጾትና ቁጥር አመልካች ምእላዶች ምን ምን እንደሆኑ ከማብራሪያ ጋር ያቀረበ ሲሆን፣ ማብራሪያው ለማርኛ ቋንቋ ገለፃ መደበር አስተዋጽኦ ሊያደርጉ የሚችሉ አንዳንድ እውነታዎች ይገኙበታል።

## ማውጫ


ገጽ

ምስጋና ..... i

አጠቃሎ ..... ii

ምእራፍ 1 መግቢያ ..... 1

1.1. የጥናቱ መነሻ ችግር ..... 1

1.2. የጥናቱ ዓላማ ..... 2

1.3. የጥናቱ ተጠቃሚዎች ..... 2

1.3.1. ተማሪዎች ..... 3

1.3.2. መምህራን ..... 3

1.3.3. መርሐ ትምህርት ነዳፊዎችና ማስተማሪያ መፃህፍት አዘጋጆች ..... 4

1.3.4. ሥነ ዘዴ አመንጪዎች ..... 4

1.4. የጥናቱ ወሰን-ስፋትና ገደብ ..... 4

1.5. የጥናቱ ዘዴ ..... 5

1.6. የጥናቱ መሰምት ..... 6

1.7. ምህፃረ-ቃላት ..... 6

ምእራፍ 2 የተዘማጅ ጽሁፎች ምልከታ ..... 7

አጭር መግቢያ

2.1 ሥነ-ምእሰድ ..... 7

2.1.1. አመጣጡ ..... 7

2.1.2. ምንነቱ ..... 10

2.1.3. የምዕሰድ ዓይነቶች ..... 10

2.2. ያማርኛ መደብ፣ ጾትና ቁጥር አመልካች ምዕላዶች ..... 11

2.2.1. ጾትና መደብ አመልካች ቅጥያዎች ..... 11

2.2.1.1. አከፋፈልን አስመልክቶ ..... 11

2.2.1.2. ፍቺን አስመልክቶ ..... 12

2.2.1.3. የምዕላዶቹን ዓይነት አስመልክቶ ..... 14

2.3. ያማርኛ መደብ፣ ጾትና ቁጥር አመልካች ምዕላዶች በመደበኛውና በዘሬው ያማርኛ አውድ ..... 15

2.3.1. ግሳውያን ቅጥያ ምዕላዶች ..... 15

2.3.2. ስማውያን ቅጥያ ምዕላዶች ..... 28

2.3.2.1. ዘረፋውያን ..... 29

2.3.2.2. መስተአምራን ..... 29

2.3.2.3. ቁጥር አመልካቾች ..... 30

ምእራፍ 3 የጥናቱ ዘዴ ..... 32

3.0. አጭር መግቢያ ..... 32

3.1. የመረጃ ምንጮች ..... 32

3.2. የመረጃ ምንጮች አመራረጥ ..... 32

3.2.1. የቦታ አመራረጥ ..... 32

3.2.2. የትምህርት ቤት አመራረጥ ..... 33

3.2.3. የክፍል (የግሬድ)አመራረጥ ..... 34

3.2.4. ምድብ አመራረጥ ..... 34

3.3. የመረጃው መሰብሰቢያ ዘዴና

ያሰባሰቡ ሂደት ........ 35

3.3.1. መረጃው የተሰበሰበበት ዘዴ ........ 35

3.3.2. የመረጃው አሰባሰብ ሂደት ........ 36

3.3.2.1. ቅድመ ፈተናዎች ........ 36

3.3.2.2. የችግሩ መፍቻ ስልት ትውውቅ ........ 37

3.3.2.3. ድኅረ-ፈተናዎች ........ 37

3.3.3. የፈተናዎቹ አወጣጥ ........ 37

3.3.4. የተፈናዎች አስተራረም የውጤት ........ 37
አመዘጋገብና አደረጃጀት ........ 39

3.3.5. የመረጃው አተናተንና ድምዳሜ አደራረስ.. 40

ምዕራፍ 4. ያማርኛ መደብ፣ ጾትና ቁጥር አመለካች ቅጥያዎችን ማስተማሪያ ስልት (ቅመስ) ........ 42

4.1. ማብራርያ ........ 42

4.2. የቅመስ መርሀ ........ 44

4.3. ሊያጋጥሙ የሚችሉ ችግሮችና መፍትሔዎቻቸው ........ 46

4.4. የመረጃው ትንተና ........ 49

4.4.1. የመረጃው አመዳደብ ........ 49

4.4.2 የመረጃው አጠቃላይ መልክ ........ 51

4.4.3 የቅመመና የድመመ ንጽጽር ........ 52

ምእራፍ 5 ጭምቅ ሃሳብ (Summary)፣ ማጠቃለያ (Conclusion) እና ጠቋሚ አስተያየት (Recommendation) ........ 56

5.0 አጭር መግቢያ ........ 56

5.1 ጭምቅ ሃሳብ ........ 56

[illegible] ማጠቃለያ ........ 65

[illegible] ጠቋሚ አስተያየት ........ 67

ዋቢ መጻሕፍት ........ 69

አባሪዎች ........ 74

## የገበታዎች ዝርዝር


ገበታ ገጽ

1. በአሁንና በትንቢት ጊዜያት መደብ፣ ጾትና ቁጥር አመልካች ቅጥያ ምዕላዶች ........ 16

2 በየዋህ ኃላፊ ጊዜ መደብ፣ ጾትና ቁጥር አመልካች ቅጥያ ምዕላዶች 17

3. በቅርብ ሃላፊ ጊዜ መደብና ጾት አመልካች ቅጥያ ምዕላዶች ........ 18

4. በሩቅ ሃላፊ ጊዜ መደብ፣ ጾትና ቁጥር አመልካች ቅጥያ ምዕላዶች ........ 19

5. በትእዛዛዊና በመጠይቃዊ አንቀጻት መደብና ጾት አመልካች ቅጥያ መዕላዶች ........ 20

6. በተሸጋሪ ግስ መደብ፣ ጾትና ቁጥር አመልካች የሆኑ የተሰቢ አጸፋዎች ........ 21

7. ባለንብረትንና ባለድረጊትን አመልካች ቅጥያ ምዕላዶች........ 22

8 ከግዕዝ አብዢ ምዕላዳት ጥቂቶቹ ........ 23

9 የመደብና የጾት አመልካች ምዕላዳት ማጠቃለያ ... 24

## የሠሌዳዎች ዝርዝር

ሠሌዳ ገጽ

1. በቀደምት ፀሃፍት የቀረቡ መደብ አመልካች ምዕሰዶች ........ 14
2. የፈተናዎች ይዘትና ቅርጽ ........ 38
3. የቅመመና የድመመ መጠነ-ተማከሎ (mesure of central tendency) ንጽጽር ........ 52
4. በድመመና በቅመመ ልዩነት "ለ" ላይ የ"ፐ" ዋጋ ........ 54
5. የፈተናዎቹ የርስበርስ ተዛምዶ (Correlation Coefficients) ........ 62
6. በቅድመ ፈተናዎች የተገኘው ማርክ ድግሞሞሽና አንፃራዊ ድግግሞሽ ........ 63
7. በድኅረ-ፈተናዎች የተገኘው ውጤት ድግግሞሽና በአንፃራዊ ድግግሞሽ ........ 64

## የግራፎች ዝርዝር


| ግራፍ | ገጽ |
|---|---|
| 1. የ"Time series" ሞዴል ማነፃፀሪያ መስመሮች | 40 |
| 2. የቅመመና የድመመ አጠቃላይ መልክ | 51 |
| 3. የቅመመና የድመመ ንጽጽር በ"Time Series Design" የንጽጽር ዘዴ | 53 |

# የአባሪዎች ዝርዝር


አባሪ — ገጽ

1 ለተማሪዎች የተሰጡ ስድስት ተከታታይ (3 ቅድመ- እና 3 ድኅረ) ፈተናዎች ........ 74

2 ጥሬ መረጃ (Row Data) ........ 92

3 Summations Obtaind from the data collected ........ 95

4. ማረጋገጫ ........ 96

## ምዕራፍ 1፡ መግቢያ

### 1.1. የጥናቱ መነሻ ችግር

የሥነ-ልሳን እውቀት ማስጨበጥ በሁሉ ወቅት ከ2ኛ ደረጃ ያማርኛ ትምህርት ዓላማዎች አንዱ ሆኖ ይገኛል። በአፀደሀፃናትና መደበኛ ትምህርት ዋና ክፍል የአማርኛ ትምህርት ቡድን (1984፤1985) ያሳተማቸው የአማርኛ መርሐ-ትምህርቶችና መማሪያ መጽሐፎች ይህን ያሳያሉ። በዲስ መልክ የተዘጋጁት እነዚህ መርሐ-ትምህርቶችና መማሪያ መጽሐፎችን ምዕላድነክ መልመጃዎችንና ክንወናዎችን በይዘትነት ይዘዋል። የምዕላድ ማስተማሪያ የሆነውን ብልሃት ግን አልያዙም።

የሥነ-ልሳን አካል የሆነው የምዕላድ ጥናት የራሱ የሆነ ዓለማቀፋዊ ማስተማሪያ ብልሃት እንዳለው ይታወቃል። ታወቂ የሥነ-ልሳን ሊቃውንት እ.ኤ.አ. በ1886 ዓ.ም. ጉባኤ አድርገው የመሠረቱት ዓለም አቀፍ የድምፅ ጥናት ማኅበር፣ ዓለም አቀፍ ፊደል /IPA/ን አውጥቷል። ይህ ፊደል ለማንኛውም የንግግር ቋንቋ የድምፀ-ልሳን መተንተኛና የምዕላድ ማስተማሪያ ሆኖ ይሠራበታል። በማርኛ ቋንቋ የምዕላድ እውቀት በትምህርትነት ሲቀርብ በለምአቀፍ ደረጃ የሚሰራበት ማስተማሪያ ብልሃቱም (ቢቻል ሀገርኛ መልክ ይዞና ከትምህርቱ ደረጃ ጋር ተጣጥሞ) አብሮ መቅረብ ነበረበት።

ይህ ባለመሆኑ የትምህርቱ ዓላማ ግብ ሊመታ ከሚችልባቸው ወሳኝ ጉዳዮች አንዱ ተጓድሎ ይገኛል።

የቋንቋ ትምህርት ዓላማ ግብ ሊመታ ከሚችልባቸው መሠረታውያን ጉዳዮች ውስጥ ተገቢ ይዘትና ተስማሚ ማስተማሪያ ዘዴ ወሳኝነት እንዳላቸው ይታመናል። አንዱ ያለንዱ አይሆንም። ይዘት ያለ ዘዴ ፋይዳ አይኖረውም፤ ዘዴም ያለ ይዘት ባዶ ነው (ሪቻርድስና ሮጀርስ፤ 1986)። በሀገራችን የምዕላድ ትምህርት ከማስተማሪያ ብልሃቱ ተነጥሎ መቅረቡ ለዚህ ጥናት መነሻ የሆነ አሳሳቢ ችግር ነው። ችግሩ ታውቆ መፍትሔ ሊፈለግለት የሚገባ ሆኖ ሳለ እስከሁን በዚህ ረገድ የተደረገ ጥናትና የተሰዘነረ መፍትሔ አላጋጠመም። በመሆኑም በር ለመክፈትና ጥሪ ለማሰማት ያህል ይህ ጥናት ቀርቧል።

## 1.2 <u>የጥናቱ ዓላማ</u>

የሀገራችንን ሥርዓተ-ፊደል በመጠቀም የአማርኛ ጸት፣ መደብና ቁጥር አመልካች ቅጥያ ምዕላዶችን በከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውስጥ ለማስተማር የሚቻልበትን አንድ ብልሃት ማቅረብ የዚህ ጥናት ዋንኛ ዓላማ ነው።

## 1.3 <u>የጥናቱ ተጠቃሚዎች</u>

የዚህ ጥናት ተጠቃሚዎች የሚከተሉት ይሆናሉ የሚል እምነት አለ፤

### 1.3.1 ተማሪዎች

የአማርኛ ተማሪዎች ቅጥያ ምዕላዶችን ለመረዳትና ከቃል ላይ ለመለየት የሚታገዙበት ብልሃት ሊያገኙ ስለሚችሉ የዚህ ጥናት ቀጥተኛ ተጠቃሚዎች ናቸው። የምዕላድ ትምህርት የሥነ-ልሳን ትምህርት አካል ነው። መሠረታዊ የሥነ-ልሳን እውቀት ማስጨበጥም በሁኑ ወቅት ከአምስቱ የአማርኛ ትምህርት ዓላማዎች አንዱ ሆኖ መቅረቡን ትምህርት ሚኒቴር ከ1984 ዓ.ም ወዲህ ከ9ነኛ-12ኛ ክፍል በወጣቸው መርሐ ትምህርቶችና መማሪያ መጽሐፎች ላይ ገልጿል። በዚህ ጥናት ለማመንጨት የሚሞከረው የቅጥያ ምዕላዶች ማስተማሪያ ብልሃት ይህ ዓላማ ግቡን እንዲመታ እገዛ ያደርግ ይሆናል።

### 1.3.2 መምህራን

የአማርኛ መምህራን ትምህርቱን ሳቢና ተስቢ አድርገው ለማቅረብ መደበኛው ያማርኛ አፃፃፍ ይፈጥርባቸው የነበረውን ችግር የሚቀርፉበትን አንድ ስልት ማግኘት ብቻ ሳይሆን ለችግሩ የየራሳቸውን የተሻለ አማራጭ ለማቅረብ መነሻ ሊሆናቸውም ይችላል።

### 1.3.3 መርሐ-ትምህርት ነደፊዎችና የማስተማሪያ መጻሕፍት አዘጋጂዎች

መርሐ-ትምህርቶችና ማስተማሪያ መጽሐፎች የትምህርቱ ዓላማ ግቡን እንዲመታ ተማሪውንና መምህሩን የሚያግዙ መሳሪያዎች እንደመሆናቸው በትምህርቱ ሂደት ላይ ለሚያጋጥሙ ችግሮች የመፍትሔ ሃሳቦችን መጠቆም ይጠበቅባቸዋል። የተወሰኑ ችግሮችን ለመፍታት ታልመው የሚቀርቡ ይህን መሰል ጥናቶች ለመርሐ-ትምህርት ነደፊዎችና ለማስተማሪያ መጻሕፍት አዘጋጂዎች የሚሰጡት ጠቀሜታ ቀላል አይሆንም። በመፍትሔነት ለሚያቀርቧቸው ሃሳቦች ምንጭና አማራጭ በመሆን ሊያግዟቸው ይችላሉ።

### 1.3. ሥነ - ዘዴ አመንጪዎች

የመማር ማስተማር ሂደት እየሰመረ የሚመጣው የማስተማር ዘዴን ለማሻሻል የማያቋርጥ ጥረት ሲደረግ እንደመሆኑ ይህ ጥናት ለሌላ ጥናት መነሻ ሊሆን ችሏል።

### 1.4 የጥናቱ ወሰን - ስፋትና ገደብ

ይህ ጥናት ከሥነ-ምዕላድ ጋር ይጣቀሳል። ሙሉ በሙሉ ግን አያጠቃልለውም።

ከምዕላድ ዓይነቶች ውስጥ በቅጥያ ምዕላዶት ላይ ብቻ ነው ትኩረት የሚደረገው። ይሁን እንጂ እነሱንም ቢሆን

በዝርዝር የማየት ዓላማ የለም። ከአማርኛ ቅጥያ ምዕላዳት ውስጥ ጾት፣ መደብና ቁጥር አመልካች በሆኑት ላይ ብቻ በማተከር እነሱን ለማስተማር የሚያግዝ ስልት ነው ለማቅረብ የሚሞከረው።

ከአማርኛ ቅጥያ ምዕላዶች ውስጥ ጾት፣ መደብና ቁጥር አመልካች በሆኑት ላይ ብቻ ለማተከር የተፈለገበት ምክንያት እነዚህ ቅጥያዎች በቋንቋው ውስጥ በሚጫወቱት የጎላ ሚና ሳቢያ ተማሪዎችን በብዛት ያጋጥማሉ፤ ከሚፈጽሟቸው የቋንቋ ስህተቶች ውስጥም ሰፋ ያለውን ድርሻ ይይዛሉ በሚል ግምት ነው፤ "ጾታ መደብ፣ ቁጥር፣ ሙያ ፤ እነዚህን አለመጠበቅ በድርሰት ታላቅ ነውር ነው" (ዓለማየሁ፤ 1957:19)። በቅርቡም ዓለማየሁ (1986) ባደረጉት ጥናት ከሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች የድርሰት ስህተቶች ውስጥ ከፍተኛውን ደረጃ የያዙት የጾትና የቁጥር ስህተቶች መሆናቸውን አረጋግጠዋል።

1.5 የጥናቱ ዘዴ

ጥናቱ መለምት አመንጪ እንደመሆኑ መጠን በገለፃዊ ዘዴ ላይ የተመረከዘ ነው። የተነሳውን ችግር ከሞላ ጎደል ያቃልላል ተብሎ የሚገመት አንድ ስልት ይቀርብና ስልቱ ውጤታማ መሆን አለመሆኑን ለመለከት በተወሰኑ የ10ኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ ሙከራ ይደረጋል። ለሙከራው የተመረጠው መሣሪያ "quasi-experimental designs" የተባለው መለኪያ ዘዴ ነው። ዘዴው ሦስት ቅድመ መመዘኛዎችንና

ሦስት ድኅረ-መመዘኛዎችን በተመጠነ የጊዜ ልዩነት ለተማሪዎች በመስጠት የቀረበው ስልት ፋይዳ ሊያስገኝ መቻል አለመቻሉን ለመተንበይ የሚረዳ ነው። መሣሪያው በመማሪያ ክፍል ውስጥ ለሚደረግ የቋንቋ ትምህርት ጥናት የተሻለ አማራጭ ነው ተብሎ ይገመታል። ዝርዝር አሠራሩ በምዕራፍ ሦስት ይቀርበል።

## 1.6 የጥናቱ መላምት

በለአንድ አቅጣጫ የሆነው የጥናቱ መላምት "በዚህ ጥናት የቀረበው የቅጥያ መለያ ስልት (ቅመስ) ለተማሪዎች ጠቀሜታ አይኖረውም፣ ወይም ይብስ ያደናግራቸዋል" የሚል ሲሆን አማራጩ ሃሳብ ደግሞ "ስልቱ ጠቀሜታ አለው" የሚል ነው።

## 1.7 ምህፃረ - ቃላት

ድግ = ድግግሞሽ

አድግ = አንፃራዊ ድግግሞሽ

ፈ = ፈተና

ድመመ = ድኅረ-መመዘኛ መረጃ

ቅመመ = ቅድመ-መመዘኛ መረጃ

ቅመስ = ቅጥያ መለያ ስልት

እ ኤ.አ = እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር

# ምእራፍ 2 የተዘማጅ ፅሁፎች ምልከታ

## 2.0 አጭር መግቢያ

ኢቃል ለዋጭ የሆኑ ያማርኛ ቅጥያ ምዕላዶችን አስመልክቶ እስከሁን ምን ተሰርቷል? ምዕላዶቹስ የትኞቹ ናቸው? የሚሉት ጥያቄዎች በዚህ ምዕራፍ ይተከርባቸዋል። በመሆኑም ከምዕላድ ምንነት በመነሳት ያማርኛ መደብ፣ ጾትና ቁጥርን አስመልክቶ የቀረቡ ሥራዎችን ለመቃኘትና ምዕላዶቹን በዝርዝር ለማየት ይሞከራል።

## 2.1 ሥነ-ምእላድ

በሥነ-ልሳን ውስጥ የምዕላድ ጥናት ሥነ-ምዕላድ በመባል ይታወቃል።

### 2.1.1 አመጣጡ

የቋንቋ ጥናት ከየት መጀመር አለበት፡ ለሚለው ጥያቄ በስነ-ልሳን እድገት ታሪክ ውስጥ ሁለት የተለያዩ መልሶች ቀርበዋል። አንደኛው ከስር ከድምፅ መጀመር አለበት የሚል ሲሆን ሁለተኛው ከላይ ከአረፍተ-ነገር መጀመር አለበት የሚል ነው። የመጀመሪያውን ሃሳብ ያቀረቡ ፍራንዝ ቦአስ ሲሆኑ ሁለተኛውን ሃሳብ ያመጡ ኖአም ቾምስኪ ናቸው።

ሁለቱ ሃሳቦች የቀረቡት በስፈ የዘመን ልዩነት ነው። ሆኖም የትኛው ትክክል ነው የሚል ጥያቄ እዚህ አናነሰም። ምክንያቱም የቋንቋ ጥናት ወይም ትንተና ከሥር ተጀመረ ከላይ የምእለድ ጥናት በሚይዘው ቦታ ላይ የሚያመጣው ለውጥ ባለመኖሩ ነው። ከስር ከድምጽ ጀምረን ወደላይ ወደአረፍተ-ነገር ብንሄድ፣ ወይም ከላይ ከአረፍተ-ነገር ተነስተን ወደታች ወደ ሥነ-ድምፅ ብንመጣ፣ የሥነ-ምዕለድ መገኛ እመከከል ላይ ከመሆን አያልፍም።

ታሪከዊ አመጣጡ ከየትኛው ነው? ስንል ግን ከለይ ሳይሆን ከሥር፣ ከረፍተ-ነገር ትንተና ሳይሆን ከድምፅ ጥናት ሆኖ እናገኘዋለን። በበርከታ እውቅ ምሁራን ርብርቦሽና በተለይም በብሉምፊልድ ብርቱ ጥረት በ1933 ዓ.ም ወደ መዋቅራዊነት ተሸጋግሮ ዘመናዊነትን መለበሱ የሚነገርለት ሥነ-ልሳን ራሱ የተገኘው የድምፅ ጥናት ውጤት ከሆነው ከገለጭ ሥነ-ልሳን መሆኑን በርከታ ፀሃፊዎች ዘግበዋል፤ ከነዚህ ውስጥ እስተርን (1983)፣ ኢስትማን (1978)፣ ቶምምከርትሁር (1990) ይገኙበታል። በተለይ ክሮል (1978) ያቀረቡት ጥናታዊ ዘገባ ሰፋ ያለ ማብራሪያ አለው፤ ሃሳቡ በጭር ተወስዷል፤

ክሮል (1978:5-12) እንደሚሉት ሰር ዊልያም ጆንስ የተባሉ እንግሊዛዊ በ1786 ዓ.ም የተወሰኑ ቋንቋዎችን ዝምድና በማጥናት ሰንስከሪት የተባለውን የጥንታዊ ቋንቋ ምንጭ ጠቆሙ፤ አውሮጳውያን የቋንቋ ጠበብት ጥናቱን ቀጥለውበት

በሥነ-ድምፅና በሥነ-ኪነ-ድምፅ ጥናቶች ውጤት ላይ ለመድረስ ስለተቻለ የገለጭ ሥነ-ልሳን ጠበብት ወደ ለጣቂ የጥናት ደረጃ ተሸጋገረው ሥነ-ምዕላድ (Morphology) የተባለውን የጥናት ዘዴ አዳበሩ።

### 2.1.2 ምንነቱ

ላንጋከር (1967:75) ምዕላድን ሲፈቱ "አነስተኛው ለዋለዋዊ መዋቅር ነው" ይላሉ። እስፖልስኪም (1978:86) "ምዕላድ፣ ፍቺ ሰጪ የቋንቋ አካል ነው" ብለዋል። ያማርኛን ለዋለው በማርኛ ቋንቋ ከፃፉ ኢትዮጵያውያን መካከል የምዕላድን ወሰነ ፍቺ ያቀረቡ ኃይሉ (1966) እና ባዬ (1987) ብቻ ናቸው። ኃይሉ(1966:10)«ምዕላድ ፍቺ የሚሰጥ በጽሑፍም ሆነ በአጠራር በመገነጣጠል ፍቺ ያላቸው ሌሎች ቀሀዶችን የማያስገኝ የድምፀ-ልሳን ስብስብ ነው »ሲሉ ባዬም (1986:49)በተመሳሳይ ሆኔታ« ምዕላድ ትርጉም አዘል የሆነና አነስተኛ ወደሆኑ ትርጉም አዘል ክፍሎች ሊከፈል የማይችል የመጨረሻው ንዑስ አሃድ ነው» ብለዋል።

### 2.1.3 የምዕላድ አይነቶች

ሁለት የምዕላድ ዓይነቶች አሉ፤ ቃለዊና ሰዋሰዋዊ ምዕላድ (Lexical and Grammatical Morpheme) ወይም ነፃ ምዕላድና እሥር ምዕላድ (Root and Affix)በማለት የተለያዩ ድርሰናት በተለያዩ ስያሜዎች ይጠራቸዋል።

ቃለዊ፣ ወይም ነፃ የተባለው የምዕለድ ዓይነት ራሱን ችሎ የሚቆም ወይም በቁሙ ፍቺ የሚሰጥ ሲሆን ሰዋሰዋዊ፣ እሥር ወይም ቅጥያ የሚባለው ምዕለድ ግን ራሱን ችሎ የማይቆምና ብቻውን ፍቺ የማይሰጥ ነው።

የዚህ ጥናት የቅርብ ዝምድና ከምዕለድ ጋር ቢሆንም ቃለዊና ነፃ የተባሉትን ራሳቸውን ችለው የሚቆሙትን ያማርኛ ምዕለዶችን አያያቸውም። ሰዋሰዋዊ፣ እሥር ወይም ቅጥያ የተባሉትን ግን በከፊል ያቅፋል፤ ሁሉንም አያጠቃልልም። የጥናቱ ትኩረት ከአማርኛ ቅጥያ ምዕለዳት ውስጥ ጾት፣ መደብና ቁጥር አመልካቾች በሆኑት ላይ ብቻ ይሆናል።

## 2.2 ያማርኛ ጾት፣ መደብና ቁጥር አመልካች ቅጥያ ምዕለዶች

### 2.2.1 ጾትና መደብ አመልካች ቅጥያዎች

#### 2.2.1.1 አስፋፈልን አስመልክቶ

በርከታ ያማርኛ ሰዋሰው ፀሃፊዎች ጾትን ተባእታይ፣ እንስታይ፣ የወል ና ግዑዝ በማለት በአራት ይከፍሉታል (መርስኤ ኃዘን፤ 1935፡28፣ ተክለማርያም፤ 1965፡27፣ ጥላሁን፤ 1965፡43)። አንዳንድ ፀሃፊዎች ግን ይህን አከፋፈል አይቀበሉም፤ (ዓለማየሁ፤ 1957፣ ይትባረክ፤ 1966፣ ባዬ፤ 1987)። ይትባረክ፤ (1966፡23-30) ግዑዝ ጾታ የሚለውን በማስቀረት የጾትን አከፋፈል ሰስት

አድርገውታል። ዓለማየሁ (1957፡19) እና ባዬ (1987) ደግሞ "የወል" እና "ግዑዝ" የተሰኙትን በመተው "ተባዕታይ" ና "አንስታይ" የተባሉትን ብቻ ወስደው የጾትን አከፋፈል ወደ ሁለት ዝቅ ያደርጉታል። ይህ ጥናት ጾት በሁለት ብቻ ሊመደብ መቻሉን ይቀበላል።

የመደብን አከፋፈል አስመልክቶ እስከአሁን የታየ ልዩነት የለም። ሁሉም ፀሐፍት መደብ 1ኛ፣ 2ኛ፣ 3ኛ፣ ተብሎ በሰስት መከፈሉን ይቀበላሉ።

### 2.2.1.2 ፍቺን አስመልክቶ፤

የጾትን ፍቺ በተመለከተ ሦስት የተለያዩ ሃሳቦች ቀርበዋል፤ የመጀመሪያው ጾትን ከተፈጥሮ ባህሪና ከህያውነት አኳያ ይወስናል፤

ሀ በተፈጥሮ በህርዩ ወንድ የሆነ ሁሉ ጾታው "ተባዕታይ" ነው።

ለ በተፈጥሮ ባህርዩ ሴት የሆነ ሁሉ ጾታው "አንስታይ" ነው።

መ የህይወት ነፍስ የሌለው ፍጥረት ግን የወንድነት ወይም የሴትነት ባህርይ የለውምና "ግዑዝ ጾታ" ይባላል።

> ሰ የህይወት ነፍስ ያለው የፍጥረት ስም ወንድ ወይም ሴት መሆኑን የማይለይ እንደሆነ ጾታው የወል ነው። (መርስኤ ኃዘን፤ 1935:28)።

ይህን ውሰኔ ተከለማርያም (1965:27) እና ጥሰሁን (1965:43) ይደግፋሉ።

ሁለተኛው፣ ጾት፣ "ቃላት በባህርያቸው ባገኙት መለያ የሚመደቡበት" ነው ይላል፤

> ጾት በግዕዝ ቋንቋ ብዙ የተለያዩ ትርጉሞች አሉት ከብዙዎቹ አንዱ ወገን ነገድ መሆኑን የሚገልፀው ፍቺ ነው። አመጣጡም ጾተ ወይም ጸወተ ወይንም ጾተወ ወገን ሆነ ከሚለው ግስነው።... የወገንን ምደበ ከፍል ስለሚያመለከት ብቻ የሰዋሰው ደራሲያን ቃላትን በስማቸውና በባህርያቸው ባገኙት መለያ ከፋፍለው ወንዴ ጾታ፣ ሴቴ ጾታ፣ አያሉ የወንድ ወገን የሴት ወገን መመደቢያ መለያ [illegible] (ደትባረከ፤1966:23)።

ሰስተኛው ጾትን ሰዋሰዋዊ ባህሪ ያደርገዋል (በዬ፤ 1987:75)። ይህ ጥናት ጾት ከተፈጥሮ ባህርይ፣ ወይም ከህያውነት አኳያ ሳይሆን ከሰዋሰዋዊ አገባብና ከቋንቋ አጠቃቀም አንፃር መፈታቱን ይቀበለል። ጾታ የሚለውንም ቃል "SEX" ለሚለው በመተው "GENDER" የሚለው እሰቤ በዚህ

ጥናት ጾት በሚል አዲስ አሰተኔ ቃል ቀርቢል።

መደብን በሰስት ከፍሎ ከማቅረብ በስተቀር እስከቅርብ ጊዜ ድረስ ፍቺው ይህ ነው ብሎ በማርኛ ቋንቋ የፃፈ አልነበረም። በቅርቡ ግን ባዬ(1987፡85) መደብ "በንግግር ወቅት፣ የሰዎች ሚና ተናጋሪነት፣ ተነጋሪነት ወይም አድማጭነት እና አንዳንድ ጊዜም ታዛቢነት" ከመሆኑ ጋር የተገናዘበ "ባህሪ" ነው የሚል ማብራሪያ አቅርበዋል።

### 2.2.1.3 <u>የምዕሰደቹን ዓይነት አስመልክቶ፤</u>

**አብዛኞቹ ያማርኛ ሰዋሰው ፀሐፊዎች "የባለቤትና የተሰቢ አፀፋዎች" ወይም "ዝርዝሮች" እያሉ ከሞሰጎደል የሚከተሉትን አቅርበዋል፤ (መርስኤኃዘን፤ 1935፣ ይትባረክ** 1966፣ ተክለማርያም ፤1965፣ ጥሰሁን፤ 1965)።

ሠሌዳ 1- <u>በቀደምት ፀሃፍት የቀረቡ መደብ አመልካች ምዕሰዶች</u>

| | | 1ኛ መደብ | 2ኛ መደብ | 3ኛ መደብ |
|---|---|---|---|---|
| | ተባዕታይ | ሁ | ህ | ግዕዝ፡ራብዕ |
| ነጠላ | እንስታይ | ሁ | ሽ/ሺ | ች |
| ብዙ | የወል | ን | አችሁ | አቸው፡ካዕብ (የሰም) |

## 2.3. ያማርኛ መደብ፣ ጾትና ቁጥር አመልካች ምዕላዶች በመደበኛውና በዘሬው ያማርኛ አውድ

ዋናው ምንጭ ቋንቋው ራሱ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ ቀጥሎ የቀረቡት ምዕላዶች ከሚከተሉት ምሁራን ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል ተወስደዋል፤ መርስኤ አኅዘን (1958:18) ተክለማርያም (1958:5)፣ ጥላሁን (1965:51) ይትባረክ (1966:74)፣ ባዬ (1987:87)፣ ቤንደርና ተባባሪዎቹ (1976:86)። ባቀራረብ ላይ ወይም ለየምዕላዶቹ በተሰጠው ትንታኔ ላይ ድክመት ቢኖር ግን ሃላፊነቱ ያጥኚው እንጂ የምሁራኑ አይሆንም።

### 2.3.1 ግሰውያን ቅጥያ ምዕላዶች

ባማርኛ ግሶች ላይ እየተቀጠሉ መደብ ጾትና ቁጥር የሚያመለክቱ ምዕላዶች በሚከተሉት ገበታዎች ቀርበዋል፤

ገበታ 1. <u>በአሁንና በትንቢት ጊዜያት መደብ ጾታና ቁጥር ለመለየት ቅጥያ ምዕላዶች</u>

| መደብ | ቁጥር | ጾታ | የትንቢት ጊዜያት ግስ | ግሱ የተነገረበት ስልት | መደብ ጾታና ቁጥር ለመለየት ቅጥያ ምዕላዶች በባለቤት አጸፋነት: መነሻ ቅጥያ | መድረሻ ቅጥያ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1ኛ | ነጠላ | — | አ—ሰብር—ኣለ—ሽሁ<br>ኣ—ለ—ሰብር—ም | ኣወንታ<br>ኣሉታ | አ— | —ሽሁ |
| | ብዙ | — | እን—ሰብር—ኣለ—ሽን<br>ኣ—ን—ሰብር—ም | ኣወንታ<br>ኣሉታ | እን—<br>ን— | —ሽን |
| 2ኛ | ነጠላ | ተባእ ታይ | ት—ሰብር—ኣለ—ሽህ<br>ኣ—ት—ሰብር—ም | ኣወንታ<br>ኣሉታ | ት—<br>ት— | —ሽህ |
| | ነጠላ | አንስ ታይ | ት—ሰብር—ኢይ—ኣለ—ሽሽ<br>ኣ—ት—ሰብር—ኢ—ም | ኣወንታ<br>ኣሉታ | ት— | —ኢይ—ሽሽ |
| | ብዙ | — | ት—ሰብር—ኣለ—ኣችሁ<br>ኣ—ት—ሰብር—ኡ—ም | ኣወንታ<br>ኣሉታ | ት—<br>ት— | —ኣችሁ<br>—ኡ |
| 3ኛ | ነጠላ | ተባእ ታይ | ይ—ሰብር—ኣለ<br>ኣ—ይ—ሰብር | ኣወንታ<br>ኣሉታ | ይ—<br>ይ— | —<br>— |
| | | አንስ ታይ | ት—ሰብር—አለ—ሽች<br>ኣ—ት—ሰብር—ም | ኣወንታ<br>ኣሉታ | ት—<br>ት— | —ሽች<br>— |
| 2ኛ ና 3ኛ | ብዙና ያክበሮት | — | ይ—ሰብር—ኣለ—ኡ<br>ኣ—ይ—ሰብር—ኡ—ም | ኣወንታ<br>ኣሉታ | ይ—<br>ይ— | —ኡ<br>—ኡ |

ገበታ 2. በየቀህ ሃሳቤ ጊዜ መደብ፣ ጾታና ቁጥር አመልካች ቅጥያ ምዕላዶች

| መደብ | ቁጥር | ጾታ | የየቀህ ሃሳቤ ጊዜ ግስ | ገሱ የተነገ ረበት ስልት | መደብ ጾታና ቁጥር አመልካች ቅጥያ ምዕላዶች በበሳቤት | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | መነሻ ቅጥያ | መድረሻ ቅጥያ |
| 1ኛ | ነጠላ | — | ሰበር—ሁ<br>አልሰበር—ሁ—ም | ካወንታ<br>ካሉታ | —<br>— | —ሁ—ኩ<br>—ሁ—ኩ |
| | ብዙ | — | ሰበር—ን<br>አል—ሰበር—ን—ም | ካወንታ<br>ካሉታ | —<br>— | —ን<br>—ን |
| 2ኛ | ነጠላ | ተባእታይ | ሰበር—ህ—(ክ)<br>ካል—ሰበር—ህ—ም | ካወንታ<br>ካሉታ | —<br>— | —ህ—(ክ)<br>—ህ—ክ |
| | ነጠላ | አንስታይ | ሰበር—ሽ<br>አል—ሰበር—ሽ—ም | ካወንታ<br>ካሉታ | —<br>— | —ሽ<br>—ሽ |
| | ብዙ | — | ሰበር—ኣችሁ<br>ካል—ሰበር—ኣችሁ—ም | ካወንታ<br>ካሉታ | —<br>— | —ኣችሁ<br>—ኣችሁ |
| 3ኛ | ነጠላ | ተባእታይ | ሰበር—ኧ<br>ካል—ሰበር—ኧ—ም | ካወንታ<br>ካሉታ | —<br>— | —ኧ<br>—ኧ |
| | | አንስታይ | ሰበር—ኧች<br>ካል—ሰበር—ኧች—ም | ካወንታ<br>ካሉታ | —<br>— | —ኧች<br>—ኧች |
| 2ኛና 3ኛ | ብዙና የክብሮች | — | ሰበር—ኡ<br>ካል—ሰበር—ኡ—ም | ካወንታ<br>ካሉታ | —<br>— | —ኡ<br>—ኡ |

ገበታ 3. በ ቅርብ ኀላፊ ጊዜ መደብና ጾታ አመልካች ቅጥያ ምዕላዶች

| መደብ | ቁጥር | ጾታ | የ ቅርብ ኀላፊ ጊዜ ግስ | ግሡ የተነገረበት ስልት | መደብና ጾታ አመልካች ቅጥያ ምዕላዶች በባለቤት አፀፋነት | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | መነሻ ቅጥያ | መድረሻ ቅጥያ |
| 1ኛ | ነጠላ | — | ሰበር—ኩ—አል—ኸሁ<br>አል—ሰበር—ሁ—ም | ግሡ የተነገረበት ስልት | —<br>— | -ኩ<br>-ሁ |
| | ብዙ | — | ሰበር—ኸን—አል<br>አል—ሰበር—ን—ም | አወንታ<br>አሉታ | —<br>— | -ኸን<br>-ን |
| 2ኛ | | ተባእታይ | ሰበር—ኸህ—አል<br>አል—ሰበር—ህ—ም | አወንታ<br>አሉታ | —<br>— | -ኸህ<br>-ህ |
| | | አንስታይ | ሰበር—ኸሽ—አል<br>አል—ሰበር—ሽ—ም | አወንታ<br>አሉታ | —<br>— | -ኸሽ<br>-ሽ |
| 2ኛ ና 3ኛ | ብዙና ያከበርት | — | ሰበር—ኸው—አል<br>አል—ሰበር—ኹ—ም | አወንታ<br>አሉታ | —<br>— | -ኸው<br>-ኹ |
| 3ኛ | ነጠላ | ተባእታይ | ሰበር—አ—አል<br>አል—ሰበር—አ—ም | አወንታ<br>አሉታ<br>አሉታ | —<br>—<br>— | -አ<br>-አ |
| | ነጠላ | አንስታይ | ሰበር—አ—አል—ሽት<br>አል—ሰበር—ሽች | አወንታ<br>አሉታ<br>አሉታ | —<br>—<br>— | -አ<br>-አች |

ገበታ 4. ብሩቅ ሀላፊ ጊዜ መደበኛ፣ጾታና ቁጥር አመልካች ቅጥያ ምዕላዶች

| መደብ | ቁጥር | ጾታ | የሩቅ ሃላፊ ጊዜ ግስ | ግሱ የተነገረበት ስልት | መደብ ጾታና አመልካች አመልካች ቅጥያ ምዕላዶች በባለቤት አፀፋ ነት | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | መነሻ ቅጥያ | መድረሻ ቅጥያ |
| 1ኛ | ነጠላ | — | ሰበረ_ኢ_ነበር<br>ኢሰ—ሰበር—ኩ—ም—ነበር | ኢወንታ<br>ኢሉታ | —<br>— | —ኢ/ዬ<br>—ኩ/ሁ |
| | ብዙ | — | ሰበር—እን—ነበር<br>ኢሰ—ሰበር—ን—ም—ነበር | ኢወንታ<br>ኢሉታ | —<br>— | —እን<br>—ን |
| 2ኛ | ነጠላ | ተባእ ታይ | ሰበር—እሀ—ነበር<br>ኢሰ—ሰበር—ሀ—ም—ነበር | ኢወንታ<br>ኢሉታ | —<br>— | —እሀ<br>—ሀ/ከ |
| | | አንስ ታይ | ሰበር—እሽ—ነበር<br>ኢሰ—ሰበር—ሽ—ም—ነበር | ኢወንታ<br>ኢሉታ | —<br>— | —እሽ<br>—ሽ |
| | ብዙ | — | ሰበር—ኢችሁ—ነበር<br>ኢሰ—ሰበር—ኢችሁ—ም—ነበር | ኢወንታ<br>ኢሉታ | —<br>— | —ኢችሁ<br>—ኢችሁ |
| 3ኛ | ነጠላ | ተባእ ታይ | ሰበር—ኢ—ነበር<br>ኢሰ—ሰበር—እ—ም—ነበር | ኢወንታ<br>ኢሉታ | —<br>— | —ኢ<br>—እ |
| | | አንስ ታይ | ሰበር—ኢ—ነበር<br>ኢሰ—ሰበር—እች—ም—ነበር | ኢወንታ<br>ኢሉታ | —<br>— | —ኢ<br>—እች |
| 2ኛና 3ኛ | ብዙና ያክብሮት | — | ሰበር—እው—ነበር<br>ኢሰ—ሰበር—ኡ—ም—ነበር | ኢወንታ<br>ኢሉታ | —<br>— | —እው<br>—ኡ |

ገበታ 5. በትእዛዛዊና በመጠይቃዊ ኣንቀፀት መደብና ጾታ ኣመልካች ቅጥያ ምዕላዶች

| መደብ | ቁጥር | ጾታ | የትእዛዛዊ ወይም የመጠይቃዊ አንቀጽ ግስ | ግሱ የተነገረበት ስልት | መደብና ጾታ ኣመሳካች ቅጥያ ምዕላዶች | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | መነሻ ቅጥያ | መድረሻ ቅጥያ |
| 1ኛ | ነጠላ | — | ል—ስበር<br>ኣ—ል—ስበር | ኣወንታ<br>ኣሉታ | ል—<br>ል— | —<br>— |
| | ብዙ | — | እን—ስበር<br>ኣ—ን—ስበር | ኣወንታ<br>ኣሉታ | እን—<br>—ን— | —<br>— |
| 2ኛ | ነጠላ | ተባእታይ | ስበር<br>ኣት—ስበር—· | ኣወንታ<br>ኣሉታ | —<br>— | —<br>— |
| | | ኣንስታይ | ስበር—ኢ<br>ኣት—ስበር—ኢ | ኣወንታ<br>አሉታ | —<br>— | —ኢ<br>—ኢ |
| | ብዙ | — | ስበር—ኡ<br>ኣት—ስበር—ኡ | ኣወንታ<br>አሉታ | —<br>— | —ኡ<br>—ኡ |
| 3ኛ | ነጠላ | ተባእታይ | ይ—ስበር<br>ኣይስበር | አወንታ<br>አሉታ | ይ—<br>ይ— | —<br>— |
| | | ኣንስታይ | ት—ስበር<br>ኣ—// ት//—ት—ስበር | ኣወንታ<br>ኣሉታ | ት—<br>—ት— | —<br>— |
| 2ኛና 3ኛ | ብዙና ያበበርት | — | ይ—ስበር—ኡ<br>ኣ—ይ—ስበር—ኡ | ኣወንታ<br>ኣሉታ | ይ—<br>ይ— | —ኡ<br>—ኡ |

ገበታ 6. በተሻጋሪ ግስ መደብ ጾታና ቁጥር አመልካች የሆኑ የተሳቢ ለጣፊዎች

| መደብ | ቁጥር | ጾታ | ቅጥያ ምዕላዶች | |
|---|---|---|---|---|
| | | | መነሻ ቅጥያ | መድረሻ ቅጥያ |
| 1ኛ | ነጠላ | — | — | -ኝ/-ኧኝ |
| | ብዙ | — | — | -ን/-ኧን |
| 2ኛ | ነጠላ | ተባእታይ | — | -ሀ/-ክ |
| | | አንስታይ | — | -ሽ. |
| | ብዙ | — | — | -ኣችሁ |
| 3ኛ | ነጠላ | ተባእታይ | — | -ት-ው/-ኧው |
| | | አንስታይ | — | -ኣት/-ይኣት |
| 2ኛና 3ኛ | ብዙና ያክብሮት | — | — | -ኣቸው |

ገበታ 7. ባለንብረትንና ባለድርጊትን አመልካች ቅጥያ ምሳሌዎች

| መደብ | ቍጥር | ጾታ | ድርጊትና ስም ከነዘርፉ | ዘርፋዊ ምሳሌዎች |
|---|---|---|---|---|
| 1ኛ | ነጠላ | — | መሄዴ<br>ቤቴ | — ኤ / —ዬ |
| | ብዙ | — | መሄዳችን<br>ቤታችን | — ኣችን |
| 2ኛ | ነጠላ | ተባእታይ | መሄድህ<br>ቤትህ | —ህ |
| | | አንስታይ | መሄድሽ<br>ቤትሽ | —ሽ |
| | ብዙ | — | መሄዳችሁ<br>ቤታችሁ | —ኣችሁ |
| 3ኛ | ነጠላ | ተባእታይ | መሄዱ<br>ቤቱ | —ኡ |
| | | አንስታይ | መሄድዋ/መሄዷ<br>ቤትዋ/ቤቷ | —ዋ/—ኣ |
| 2ኛና 3ኛ | ብዙና ያከበሮት | — | መሄዳቸው<br>ቤታቸው | — ኣቸው |

ገበታ ፰. <u>ከግዕዝ ኣብዢ ምስሊዓት ጥቂቶች</u>

| የነጠላ ቁጥር ስም | የብዢ ቁጥር ስም | ኣብዢው ምዕላድ |
| --- | --- | --- |
| ሰማእት | ሰማእታት | – ኣት |
| ጻድቅ | ጻድቃን | – ኣን |
| ሹም | ሹማምንት | – ኣምንት |
| ከሩብ | ከሩቤል | –ኤል |
| ቄስ | ቀሳውስት | – ኣውእት |

በግዕዝ ደንብ የብዙ ስሞች "ወደ ኣማርኛ ሲገቡ እንደ ነጠላ ቁጥር ያማርኛ ስሞች እችን ይጠምራሉ/ብዩ 1987፡ 71

ገበታ 9 የመደብና የጾታ አመልካች ምዕላዳት ማጠቃለያ

| ጾታ | መደብ | ጾታ አመልካች ቅጥያ ምእላዳት | | | | | | | በባለንብረትነት ወይም በባለድርጊትነት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | በምደብ ተውላጠስም ላይ | አውቅ በሆነ ስም ላይ | በባለቤት አፀፋነት | | | | በተሳቢ አፀፋነት | |
| | | | | በ ሃላፊ ጊዜ | በኢ ሃላፊ ጊዜ | በትዕዛዝ አንቀጽ | በቦዝ አንቀጽ | | |
| አንስታይ | 2ኛ | -ኢ | - | -/ኧ/ሽ | ት-ኢ-ኧሽ | -ኢ | -ኧሽ | -ሽ | -/አ/ሽ |
| | 3ኛ | -ኣቷ/-ዋ | -ዋ<br>-ኢት-ኡ | -ኧች | ት- -ኧች | -ት- | -ኣ ዋ | -ኣት | -ኣቷ/-ዋ |
| ተባእታይ | 2ኛ | -ኧ | - | -ሀ/-ከ | ት—ኧሀ | ...Ø | -ኧህ | -ሀ | -/ኧ/ሀ |
| | 3ኛ | -ኡ | -ኡ | -ኧ | ይ- | ይ- | -ኦ | -ው<br>-ት | -ኡ/-ው |

23

በአሁንና በትንቢት ጊዜያት /እ(ል)፣ን፣ት፣ይ/ የሚሉ መነሻ ቅጥያዎች ይገኛሉ። እነዚህ ቅጥያዎች መደብ አመልካች ምዕለደች ናቸው። ከ3ኛ መደብ፣ ነጠላ ቁጥር፣ ተባእታይ ጾትና ከ1ኛ መደብ ላይ በስተቀር በሌሎቹ ቦታዎች መነሻ ቅጥያዎች የባለቤት አፀፋዎቻቸውን ያስከትላሉ። አፀፋዎቹ የ"እ" ድምፅ አላቸው። በድድ ድምጾች የሚጨርሱ ግሶች በአሁንና በትንቢት ጊዜያት፣ 2ኛ መደብ፣ ነጠላ ቁጥር፣ እንስታይ ጾት ላይ የድድ ድምጾቻቸውን ወደ ላንቃ ድምጽነት ይለውጣሉ። ያማርኛ ግሶች ሦስት ዓይነት ቅጥያዎች ባንድ ጊዜ የሚወስዱት በአሁንና በትንቢት ጊዜያት፣ በሁለተኛ መደብ፣ ነጠላ ቁጥር እንስታይ ጾት፣ አወንታዊ ስልት ላይ ብቻ ነው።

በየዋህ ኃላፊ ጊዜ መነሻ ቅጥያዎች የሉም። መደብ፣ ጾትና ቁጥር የሚገለፀው የባለቤት አፀፋዎች በሆኑት በመድረሻ ቅጥያዎች ብቻ ነው።

በቅርብ ኃላፊ ጊዜ የሚነገሩ ግሶች መነሻ ቅጥያ የላቸውም፤ አብዛኞቹ መደብ፣ ቁጥርና ጾት አመልካች የሆኑ መድረሻ ቅጥያዎች ብቻ አሏቸው፤ ጠራ፣ ቋጣ ያሉ ግሶች ለ3ኛ መደብ፣ ነጠላ ቁጥር፣ ተባእታይ ጾት በአሉታዊ ስልት ሲነገሩ ምንም ዓይነት ቅጥያ የላቸውም። በድድ ድምጾች የሚጨርሱ ግሶች 1ኛ መደብ ነጠላ ቁጥር ላይ በአወንታ ሲነገሩ የድድ ድምጾቻቸውን ወደ ላንቃ ድምጽነት ይቀይራሉ። መድረሻ ቅጥያዎቹ -ኤ- 1ኛ መደብ ነጠላ

ቁጥር፣ -ሉ- ደግሞ ፫ኛ መደብ አንስታይ ጾት፣ ያመለክታሉ።

በሩቅ ሃላፊ ጊዜ፦ ያማርኛ ግሶች መነሻ ቅጥያ አይወስዱም፤ በአወንታም ሆነ በአሉታ፣ መደብ፣ ጾትና ቁጥር የሚገለጹት በመድረሻ ቅጥያዎች ብቻ ነው፤ ስርቻቸውን የጎረዱ ግሶች -ት- የሚል ድምፅ ያመጣሉ። በድድ ድምፅ የሚጨርሱ ግሶች በ1ኛ መደብ ነጠላ ቁጥር አዎንታ ላይ የድድ ድምጸቻቸውን ወደላንቃ ድምፅነት ይቀይራሉ።

በትእዛዛዊ አንቀጽ፦ ለ2ኛ መደብ፣ ነጠላ ቁጥር ተባእታይ ጾት ምንም አይነት ቅጥያ የለም፤ አንቀጹ ሌጣውን ይነገራል፣ በድድ ድምጾች የሚጨርሱ ግሶች በ2ኛ መደብ ነጠላ ቁጥር እንስታይ ጾት ላይ የድድ ድምጸቻቸውን ወደላይንቃ ድምጽነት ይቀይራሉ። በመጠይቃዊ አንቀጽ፣ ከ2ኛ መደብ በስተቀር፣ መደብ አመልካች የሆኑት መነሻ ቅጥያዎች ይገኛሉ።

እነዚህ አፀፋዎች ለማንኛውም ተሻጋሪ ግስና ለመሆን አንቀጽ በተለያዩ የግስ ጊዜያት የተሳቢውን (በመሆን አንቀጽ ላይ የባለቤቱን) መደብ፣ ጾትና ቁጥር ያመለክታሉ።

ከገበታ 1-9 የቀረቡ መደብ፣ ጾትና ቁጥር አመልካች ግሳውያን ቅጥያዎችን እንደሚከተለው ማጠቃለል ይቻላል፤

ሀ <u>መነሻ ቅጥያዎች</u>፦ እ-ል-፣ እን-፣ን-፣ት-፣ይ- መደብ አመልካቾች ናቸው። በኢሃሰፊ ጊዜና በትእዛዛዊና በመጠይቃዊ አንቀፃት ከ2ኛው መደብ፣ ተበእታይ ጾት በስተቀር ለሌሎቹ መደቦች እንደሁኔታው በግሱ መነሻ ላይ ይገባሉ። /እ-/ና/ል-/ 1ኛ መደብን በነጠላ ቁጥር ሲያመለክቱ /እን-/ና/ን-/ 1ኛ መደብን በብዙ ቁጥር ያሳያሉ። /ት-/ የ2ኛ መደብና የ3ኛ መደብ አንስታይ ጾት አመልካች ሲሆን /ይ-/ ደግሞ 3ኛ መደብ ተበእታይ ጾት አመልካች ነው፣ 3ኛ መደብ ብዙ ቁጥርንና አክብሮትንም ያመለክታል።

ለ. መድረሻ ቅጥያዎች:/-ኡ-ኢ-አ-ኤ-/ ቁጠርና ጾት አመልካቾች ናቸው። /-ኡ/ በሁለተኛና በ3ኛ መደቦች ላይ ብዙ ቁጥርና አክብሮትን ያመለክታል። /-ኢ-/ና/-አ-/ እንደቅደምተከተላቸው በ2ኛና በ3ኛ መደቦች ላይ አይነተኛ እንስታይ ጾት አመልካቾች ናቸው። -ኤ- ከጾት ውጪ ሆኖ 1ኛ መደብን በነጠላ ቁጥር ያመለክታል።

ሌሎቹ መድረሻ ቅጥያዎች፦ ግሱን ከስማዊ ሐረጉ ጋር በመደብ በጾትና በቁጥር የሚያመሳስሉ የባለቤትና የተሳቢ አፀፋዎች ናቸው። -ኩ-ሁ፣-ህ፣-ሽ፣-ሾ፣ና-ች በሃለፊ ጊዜ የነጠላ ቁጥር መደብ አመልካች የባለቤት አፀፋዎች ሲሆኑ ከነዚህ ውስጥ እንስታይ ጾት አመልካቾቹ ለ2ኛ መደብ -ሽ፣ ለ3ኛ መደብ ደግሞ -ች ናቸው።

-ን፣-ኣችሁ-እና/-ኡ/ እንደ ቅደምተከተላቸው በ1ኛ፣ በ2ኛና በ3ኛ መደቦች ላይ ብዙ ቁጥር ያመለክታሉ። የተሳቢ አፀፋዎቹም እንዲሁ ለ1ኛ መደብ ነጠላ ቁጥር /-ኝ/-ኧኝ/፣ ለ3ኛ መደብ እንስታይ ጾት /-ኣት(-ይ ኣት)/፣ ለ 3 ኛ መደብ ተባእታይ ጾት /-ት፣-ው(-ኧ ው)/ ሲገቡ በብዙ ቁጥር ደግሞ /-ን፣-ኣችሁ/እና/-አቸው/ እንደ ቅደም ተከተላቸው ለ1ኛ፣ ለ2ኛና ለ3ኛ መደቦች ይውላሉ። በቅርብ ሃላፊ ጊዜ በ3ኛ መደብ፣ በትእዛዝ አንቀጽ ደግሞ በሁለተኛ መደብ ላይ የተባእታይ ጾት አመልካች ቅጥያ ምዕላድ የለም። ከ2ኛና ከ3ኛ መደቦች ብዙ ቁጥር ላይ በስተቀር መድረሻ አፀፋዎች (-ኧ-)ን ሊያስከትሉ ይችላሉ።

ከዚህ በላይ ግሳውያን የሆኑ መደብ፣ ጾተና ቁጥር አመልካች ቅጥያ ምዕላዶችን ለማየት ተሞክሯል፤ ቀጥሎ ስማውያን የሆኑት ምዕላዶት ይታያሉ።

### [illegible] ስማውያን ቅጥያ ምዕላዶች

በዚህ ርዕስ ስር የምናያቸው በዘርፍነት፣ በመስተአምርነትና በቁጥር አመልካችነት በስምና በተውላጠ ስም ላይ የሚቀጠሉ ምዕላዶችን ይሆናል። ዘርፋውያን ምዕላዶች በለንብረትንና ባለድርጊትን በመደብ፣ በቁጥርና በጾት ለይተው ያመለክታሉ። መስተአምራን፣ ስማዊ ቃልን በጾት ለይተው እውቅ ያደርጋሉ። ቁጥር አመልካቾቹ ደግሞ ተቆጣሪ

ስምንና ተውሳጠ ስምን በነጠላነት ወይም በብዙነት ያመለክታሉ።

#### 2.3.2.1 <u>ዘረፋውያን</u>

ኃይሉ (1969)ና፣ ባዬ (1987:79-81) በፃፉት መሠረት፣ ዘርፍነት በተለያዩ ምዕላዳት አማካይነት የሚገለጽ፣ ከገንዘብና ከባለገንዘብነት ጋር የተያያዘ፣ የስሞች ሰዋሰዋዊ ሙያ ወይም ተግባር ሲሆን ሙያው "ባለንብረትን ብቻ ሳይሆን ባለድርጊትንም" ያሳያል።

#### 2.3.2.2 <u>መስተአምራን</u>

"መስተአምር" የሚለውን ቃል ሰዋሰዋዊ ፍቺ በማስያዝ ለመጀመሪያ ጊዜ የተጠቀሙበት አለማየሁ ሞገስ መሆናቸውን ኃይሉ (1966) ጠቁመዋል። ፍቺው እውቅ ማድረግ ማለት ነው። "እምርነት ስንል እውቅነት ማለታችን ነው" (ባዬ 1987:82)።

በማርኛ የእምርነት ምዕላዶች ሁለት ብቻ ሲሆኑ እንስም /-ኡ/ እና /-ዋ/ ናቸው። /-ኡ/ የተባእታይ ስሞች ሲሆን /-ዋ/ ያንስታይ ስሞች ነው። ሁለቱም ነጠላ ቀጥር ናቸው። በብዛኛው የሚገቡት ለ3ኛ መደብ ቢሆንም ለ2ኛና ለ1ኛ መደቦችም ይውላሉ። "አንተኛው፣ አንቺኛዋ፣ እነዚህኞቹ፣ እኔው?" የሚሉት አባባሎች ይህን ያሳያሉ። ከነዚህ ውጪ የመስተአምርነት ሙያ ባይኖረውም /-ኢት/ የሚል እንስታይ

ጾት አመልከች ሰማዊ ምዕስድ አለ።

2.3 <u>ቁጥር አመልካቾች</u>

ቁጥር ነጠላና ብዙ ተብሎ በሁለት ይከፈላል። ምናልባት ከመስተአምራን በስተቀር የነጠላነት አመልካች ምዕለድ በማርኛ ቋንቋ ውስጥ የለም። ባዩ (1987:69) ግን ይህን ሃሳብ ሰይሽሩ "አንዳንድ ስሞች ... ንጥልነትን ወይም ልይነትን የሚያመለክቱበት ምዕለድ አላቸው፤ ምዕለዱ /-እየ/ ነው" ብለው ጽፈዋል።

ባዩ (1987:70) እንደፃፉት ያማርኛ ብዙ ቁጥር አመልካች ምዕለዶች /-ኦች/እና/እነ-/ ናቸው።

| ምሳሌ 1 | ነጠላ | ብዙ |
|---|---|---|
| | ልጆች (ልጅ-ኦች) | |
| | ተማሪ | ተማሪዎች |
| | እሱ | እነሱ (እነ-እሱ) |
| | አንተ | እናንተ (-አንተ) |

-ዎች ራሱን የቻለ ምዕለድ ሳይሆን የ-ኦች ዝረ-ምዕለድ ነው። በአናበቢ ለሚጨርሱ ስሞች ይገባል። -ኦች ና እነ- ግን ተመሳሳይ ተግባር ቢያከናውኑም ራሳቸውን እንደቻሉ ምዕለዶች ተደርገው ይታያሉ። ቢሆንም ተወራራሽነት ስለሌላቸው አንዱ በሚመጣበት በታና ሁኔታ ሌላው አይመጣም። እነ- መነሻ ቅጥያ ሲሆን

/-አች/ መድረሻ ነው። /እነ-/ ተውላጠ ስሞችንና የተፀውኦ ስሞችን ሲያበዛ /-አች/ ሌሎች ተቆጣሪ ስሞችን ያበዛል። ሁለቱም በቀጥታ በሚያበዙት ስማዊ ቃል ላይ ይለጠፋሉ እንጂ በመካከከል ሌላ ቅጥያ ጣልቃ አያስገቡም።

ከነዚህ ውጪ አማርኛ ከግዕዝ ቋንቋ ከወረሳቸው ቃላት ጋር አብረው የመጡ የሚመስሉ የተለያዩ አብዢ ምዕላዶች አሉ። ዋናዋናዎቹን በገበታ 8 ይመለከቷል።

# ምዕራፍ 3 የጥናቱ ዘዴ

## 3.0 አጭር መግቢያ

በዚህ ምእራፍ ስለጥናቱ የመረጃ ምንጮች፣ ስለመረጃ መሰብሰቢያው ዘዴና ስለአሰባሰቡ ሂደት፣ እንዲሁም ስለመረጃው አተናተንና ድምዳሜ አደራረስ ስርአት ለመግለፅ ይሞከራል።

## 3.1 የመረጃ ምንጮች

ለጥናቱ የመረጃ ምንጮች እንዲሆኑ የተመረጡት በአዳማ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የ10ኛ ኤፍ ክፍል ተማሪዎች ናቸው። 34 ወንዶችና 42 ሴቶች በድምሩ 76 ተማሪዎች ጥናቱን ጀምረው ሦስቱ ሲያቋርጡ 33 ወንዶችና 40 ሴቶች በድምሩ 73 ተማሪዎች አጠናቀዋል። ከነዚህ ውስጥ 7 ወንዶችና 10 ሴቶች በድምሩ 17 ተማሪዎች (21.9%) በማርኛ ቋንቋ አፍ ያልፈቱ ናቸው። የቀሩት 26 ወንዶችና 30 ሴቶች በድምሩ 56 ተማሪዎች ደግሞ በማርኛ ቋንቋ አፍ የፈቱ ናቸው።

## 3.2 የመረጃ ምንጮች አመራረጥ

### 3.2.1 የቦታ አመራረጥ

ጥናቱን በገር አቀፍ ደረጃ ለማከሄድ ያለው የጊዜና የገንዘብ አቅም ስለልፈቀደ የተወሰነ ቦታ ተመርጦ መረጃ ተሰብስቧል። የጥናቱን ቦታ በቦሰጡኝ ዘዴ ከመምረጥ ይልቅ በምክንያት ላይ ተመርኩዞ መምረጥ የሚሻል ሆኖ በመገኘቱ ተሰርቶበታል። ዋና ዋናዎቹ ምክንያቶች ሦስት ናቸው፤ ለጥናቱ የሚመረጠው ቦታ፣ አንደኛ፣ ከገጠሩም ከከተማውም ህይወቶች የሚያጣቅስና የቅይጥነት መልክ ያለው፣ ሁለተኛ፤ በማርኛ አፍ የፈቱም ያልፈቱም ~~ያልፈቱም~~ ተማሪዎች የሚገኙበትና ሦስተኛ፦ ለጥኒውም አመቺነት ያለው እንዲሆን ተፈልጊል። ከነዚህ ምክንያቶች አኪያ ናዝሬት ከተማ ተመርጧል።

### 3.2.2 የትምህርት ቤቱ አመራረጥ

በናዝሬት ከተማ ውስጥ ሦስት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ይገኛሉ። አንደኛው የሚሲዮን ሲሆን ገንዘብ የሚያስከፍል ትምህርት ቤት ነው። ሁለተኛው የቴክኒክና ሙያ ትምህርት ቤት ስለሆነ የቀለም ትምህርት በተደራቢነት የሚሰጥበት ነው። ሦስተኛው የመንግስት ትምህርት ቤት ሆኖ ለናዝሬትና ለከባቢዋ አገልግሎት የሚሰጥ ነው። ከናዝሬት ከተማ ውጪ ውልንጪቲ፣ አዋሽመልከሰ፣ አቦምሰ፣ ባህረገሲሰ፣ ዱራና ቆቃ ከሚባሉ የገጠር ከተሞች የስምንተኛ ክፍል ብሄራዊ ፈተና አልፈው የሚመጡ ተማሪዎችን ይቀበላል። በወጡት የመምረጫ መስፈርቶች መሰረት ይህ ትምህርት ቤት ተመርጧል።

### 3.2.3 የክፍል (የግሬድ) አመራረጥ

ጥናቱ የሚካሄድበትን የክፍል ደረጃ ለመወሰን ከዘጠነኛ እስከ አስራ ሁለተኛ ክፍል አራት አማራጮች ነበሩ። ከነዚህ መካከል አንዱን ለመምረጥ አሁንም ከበሰጡኝ የመምረጫ መንገድ ይልቅ ምክንያታዊ በሆነ መስፈርት መጠቀም እንደሚሻል ታምኖበት መስፈርት ወጥቶ ተሰርቶበታል። መስፈርቱ ለሁለተኛ ደረጃ ትምህርት በተመደበው የአራት ዓመት የጊዜ መጠን ላይ የአማካይነት ቦታ ያለው የሚል ነው። ይህ መስፈርት የወጣው በአማካይ ደረጃ ላይ ከሚገኝ ~~ደረጃ ላይ ከሚገኝ~~ ምንጭ የሚወሰድ መረጃ ወደፊትም ወደኋላም ያሉትን ደረጃዎች የመወከል ባህሪ ሊኖረው ይችላል በሚል ግምት ነው። በዚህ መስፈርት መሰረት በሁለተኛ ደረጃ የትምህርት ዘመን ላይ መጀመሪያና መጨረሻ የሚገኙት ዘጠነኛና አስራሁለተኛ ክፍሎች ከውድድር ውጪ ሆነዋል። ከቀሪዎቹ ከሁለቱ ክፍሎች ይህ ጥናት ከሚካሄድበት ከጥር-ሚያዚያ ባለው የትምህርት ጊዜ ውስጥ አስረኛ ክፍል ወደ አስራአንደኛ ክፍል ቅርበት ሲያሳይ አስራአንደኛ ክፍል ደግሞ ቅርበቱ ወደ አስራሁለተኛ ክፍል ሆኖ ተገኝቷል። ስለዚህ አስረኛ ክፍል ያማካይነትን ቦታ በመያዙ መምረጫ መስፈርቱን ስለሚለ ለጥናቱ ተመርጧል።

### 3.2.4 ምድብ አመራረጥ

በአዳማ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የሚገኙ የ10ኛ ክፍል ተማሪዎች በ12 ሴክሽኖች የተመደቡ ናቸው።

ሁሉም እኩል የመመረጥ እድል እንዲኖራቸው ተብሎ ምርጫው በእጣ ሆኗል። ከትምህርት ቤቱ መምህራን አንዱ እጣውን እንዲያወጡ ተደርጎ ለ10ኛ ኤፍ ክፍል በመውጣቱ ጥናቱ በዚህ ክፍል ተማሪዎች ላይ ሊካሄድ ችሏል።

## 3.3 የመረጃው መሰብሰቢያ ዘዴና ያሰባሰቡ ሂደት

### 3.3.1 መረጃው የተሰበሰበበት ዘዴ

የጥናቱ መረጃ የተሰበሰበው በፈተናዎች ነው። ከፈተና ሌላ በጥቅም ላይ እንዲውል የተደረገ መሳሪያ የለም። የተቻለውን ያህል ጥንቃቄ ተደርጎባቸው የተዘጋጁ ስድስት ፈተናዎች በተወሰነ የጊዜ ርቀት ለተጠኚ ተማሪዎች እየተሰጡ መረጃው ተሰብስቧል። ከስድስቱ ፈተናዎች ሶስቱ ቅድመ-ስልት ፈተናዎች (Pre-tests) ሲሆኑ ሶስቱ ድህረ-ስልት ፈተናዎች (Post-tests) ናቸው። እያንዳንዱ ፈተና በአንድ ሰምንት የጊዜ ልዩነት ነው የተሰጠው። የተፈናዎቹ ብዛትና ያሰጣጡም የጊዜ ልዩነት መጠን የተወሰነው ለጥናቱ በተመረጠው 'Quasi experimental design' በተባለው ዘዴ መርህ መሰረት ነው። ይህ ዘዴ ስለተመረጠበት ምክንያት ጥቂት መግለጽ ያስፈልጋል።

ሃችና ፋርሃዲይ (1982:22) እንደፃፉት ሳይንሳዊ ጥናት የሚደረግባቸው አስተማማኝ የሙከራ መሰሪያዎች (True Experimental Designs) ሶስት መሰረታውያን ባህርያት አሏቸው፤ አንደኛ፤ የመቆጣጠሪያ ቡድን (Control group) መኖር፤

ሁለተኛ፣ የተጠኚዎች ምርጫና ምደባ ባስሰጡኝ መሆንና ሶስተኛ፣ ቡበድኖቹ መከከል ያለውን መነሻ ልዩነት ለመጨበጥ የቅድመ-ፈተና አስፈላጊነት ናቸው። ሆኖም እነዚህን መስፈርቶች በተክክል በስራ ላይ ለማዋል ገሃዱ ዓለም፣ የትምህርት ቤቶችና የመማሪያ ክፍሎች ተጨባጭ ኢውንታዎችና የቋንቋ ጥናት ውስብስብ ባህርያት አያመቹም (ሃችና ፋርሃዲይ፤ 1982:23)። በጥናቱ ሂደትና ውጤት ላይ ችግሮች ሊያጋጥሙ ይችላሉ። ለዚህ መፍትሄውና የተሻለው አማራጭ መንገድ በ'Quasi-experimental Design' መጠቀም መሆኑን ሃችና ፋርሃዲይ (1982:24) እንደሚከተለው ገልፀዋል።

> Quasi-exprimental designs are practical compromise
> between true experimentation and the nature of
> human language behavior, which we wish to investigate.
> They are also the best alternatives available to us.

በዚህ መሰረት 'Quasi-experimental design' ለዚህ ጥናት ሊመረጥ ችሏል። ይህ መሳሪያ 'Time series' እና 'Time sample' የተባሉ ሁለት ሞዴሎች አሉት በዚህ ጥናት የተሰራበት 'Time series' የተባለው ሞዴል ነው። ያሰራሩ ሂደት ቀጥሎ ቀርቧል።

### 3.3.2 የመረጃው አሰባሰብ ሂደት

#### 3.3.2.1 ቅድመ-ፈተናዎች

ለተጠኚ ተማሪዎች ሶስት ቅድመ-ፈተናዎች በንድ ሳምንት

የጊዜው ልዩነት ለሶስት ሳምንታት በተከታታይ እየተሰጡ መረጃ ተሰበሰበ።

### 3.3.2.2 የችግሩ መፍቻ ስልት ትውውቅ፤

የቅድመ ፈተናዎች አሰጣጥ ሂደት እንደተጠናቀቀ፤ በጥናቱ ለተነሳው ችግር መፍትሄ ይሆናል ተብሎ የተዘጋጀውን ስልት ተጠኚ ተማሪዎች እንዲያውቁት ተደረገ።

### 3.3.2.3 ድህረ-ፈተናዎች፤

ያዲሱ ስልት ትውውቅ ሂደት ከተጠናቀቀ በኋላ ሶስት ድኅረ ፈተናዎች ለሶስት ተከታታይ ሳምንታት ለተጠኚ ተማሪዎች ተሰጧቸው። እዚህ ደረጃ ላይ ሲደረስ የሚከተለው የጥናቱ መስሪያ ሞዴል ተጠናቋል፤

ፈ.1 ፈ.2 ፈ.3 X ፈ.4 ፈ.5 ፈ.6

### 3.3.3 የፈተናዎች አወጣጥ

ከላይ እንደተገለፀው የጥናቱ መረጃ የተሰበሰበው በቅድመ መመዘኛነትና በድህረ መመዘኛነት በተሰጡ ስድስት ፈተናዎች ነው። የፈተናዎቹን አስተማማኝነት ለማስጠበቅ የተቻለውን የሀል ጥንቃቄ ለማድረግ ተሞክሯል። የፈተናዎቹ ዓይነት ምርጫ ሳይሆን በደ ቦታ መሙላት ነው። ስድስቱም ፈተናዎች በዓለማና በይዘት አንድ ሆነው

በቅርጽ ብቻ ይለያያሉ። የፈተናዎቹ ዓላማ፣ ተማሪዎቹ ከአዲሱ ስልት በፊትና በኋላ፣ ጾታ፣ መደብና ቁጥር አመልካች የሆኑ ቅጥያ ምዕላዶችን የመረዳትና ከቃል ላይ የመለየት ችሎታቸውን መለካት ሲሆን የተፈናዎቹ ይዘቶች ጾታ፣ መደብና ቁጥር አመልካች የሆኑ ቅጥያ ምዕላዶች ናቸው። ፈተናዎቹ የሚፈለገውን ባህሪ ብቻ የሚለኩ ሆነው ይገኙ ዘንድ የይዘት ልዩነት የላቸውም። በተለያዩ ቃላት ላይ እየተለጠፉ ለስድስቱም ፈተናዎች ይዘት ሆነው የተጠየቁት ምእላዶች:- -ዎች፣ -ኦች፣ -ኣት/-ኣን፣ -ኡ፣ እኑ-፣ -ኢት፣ -ኢ፣ -ቻ፣ -ሽ ናቸው። የፈተናዎቹ መደጋገም አስተማማኝነት ያለው ውጤት ለማስገኘት ይረዳል። ሆኖም የጭውረት ተፅእኖ ሊያስከትል ስለሚችል ይህን ተፅእኖ ለመከላከል ቅጥያዎቹ የተጠየቁባቸው ቃላት በየፈተናዎቹ ይለያያሉ። የሆሄ መጠናቸውም እየጨመረ የክብደት ደረጃቸው እንዲያድግ ተደርጓል። የተፈናዎቹ ናሙና በአባሪ 1 ላይ ከገጽ 83 እስከ ገፅ 91 የቀረበ ቢሆንም የሚከተለው ሠሌዳ ስለፈተናዎቹ ይዘትና ቅርፅ አጠቃላይ ግንዛቤ ለማግኘት ይረዳ ይሆናል፤

ሠሌዳ 2. <u>የፈተናወች ይዘትና ቅርፅ</u>

| ይዘት | ፈ1 | ፈ2 | ፈ3 | ፈ4 | ፈ5 | ፈ6 |
|---|---|---|---|---|---|---|
| -ዎች | ካበዎች | ተራራዎች | ተማሪዎች | ተጠያቂዎች | ተጠባባቂዎች | ማስገንዘብያዎች |
| -ኦች | ልጆች | ደብተሮች | እርሳሶች | ብርቱካኖች | መስተዋደዶች | መስተፃምሮች |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| -ኣን/ኣት | ሙታን | ፃድቃን | ልዑላን | ከሀናት | ነቢያት | ሰማእታት |
| -ኡ | ሄዱ | ከሩ | ተማሩ | ተማከሩ | አስተባበሩ | ስሰስተ ናገዱ |
| እኑ- | እነሱ | እነሱ | እነሱ | እናንተ | እናንተ | እናንተ |
| -ኢት | ልጂት | ቆቂት | ኅበዚት | ቅምጥሊት | ግድርድሪት | ቅልብ ልቢት |
| -ኢ | ሂጂ | ሰበሪ | ተናገሪ | ተቆጣጣሪ | አስጠንቅቂ | ተምነሽነሺ |
| -ኢ | ፃፊ | ልበሺ | በርቺ | አትስጪ | አትውሰጂ | አስደስቺ |
| -ች | ጠራች | መጣች | ገበች | ገደለች | ገመገመች | አደናቀፈች |
| -ሽ | መታችሽ | ሰጠችሽ | ገፋችሽ | አመነችሽ | ጠረጠረችሽ | አስለፈለፈችን |

በተጨማሪም ፈተናዎቹ ችግሩንም እንዲለኩ ሆነው ተቀርፀዋል። በመደበኛው ያማርኛ አፃፃፍ በቃል ላይ በግልፅ የሚታዩና የማይታዩ ቅጥያ ምዕላዶች በሁሉም ፈተናዎች ውስጥ የቀረቡት ለዚህ ዓላማ ጭምር ነው።

### 3.3.4 የፈተናዎች አስተራረም፣ የውጤት አመዘጋገብና አደረጃጀት


ፈተናዎቹ የመጀመሪያ ዲግሪና የማስተማር ልምድ ባላቸው ሁለት መምህራን ታርመዋል። ትክክለኛውን መልስ የሚያሳይ ወረቀት ለራሚዎቹ ተሰጥቷል። የፈተናዎቹ ውጤት ቅድመ-ስልት ተብሎ በሁለት ተመድቦ ስለያንዳንዱ መረጃ ሰጪ የክፍል ቁጥር፣ ጾታና ያፍ መፍቻ ቋንቋ በሚያመለክት ክድ በመረጃነት ተመዝግቧል። እያንዳንዱ ተጠኚ ተማሪ በየፈተናዎቹ ትክክል ያገኘባቸውንና የተሳሳተባቸውን የጥያቄ ዓይነቶች ሊያሳይ የሚችል ቅጽ ተዘጋጅቶም

ተሰርቶበታል። በዚህ መልክ የተመዘገቡትና በያንዳንዱ ምድብ ስር የተቀመጡት የፈተና ውጤቶች በነጠለና በምድብ አማካይ ወጥቶላቸው ለትንተና ሂደት እንዲመቻቹ ተደርጓል።

### 3.3.5 የመረጃ አተናተንና ድምዳሜ አደራረስ

ሴሊገርና ሽሃሚ (1989፡159) እንደገለፁት ያንድ ጥናት ዓላማ፣ የመረጃ አሰባሰቡ ዘዴና ያተናተኑ ስርዓት የተዛመዱ ናቸው።በመሆኑም የጥናቱ የመረጃ አተናተንና ድምዳሜ አደራረስ ሂደት ለጥናቱ በተመረጠው መሰሪያ መርሀ መሰረት በድህረ-ፈተናዎችና በቅድመ ፈተናዎች የተሰበሰቡ መረጃዎችን በማነፃፀር አንድ ውጤት ላይ ተደርሷል። የተገኘው ውጤት ከጥናቱ መለምቶች አንዱን ጠቁሟል። የ'Time series' ሞዴል የማነፃፀሪያ ንድፎች የሚከተሉት ናቸው (ሃችና ፋርሃዲ.ይ፤ 1982፡25)፤

ግራፍ 1 የ'Time series' ሞዴል ማነፃፀሪያ መስመሮች




የመስመሮቹ ትርጉም እንደሚከተለው ነው (ሃችና ፋርሃዲ.ይ፤ 1982፡25)፤

መስመር 1 = አዲሱ ስልት ጠቀሜታ የለውም፤ ተማሪዎቹ ቢማሩትም ባይማሩትም ውጤታቸው ለውጥ የለውም።

መስመር ፪ = አዲሱ ስልት ይብስ ተማሪዎችን ያደናግራል፤ ጎጂ ነው እንጂ ጠቃሚ አይደለም።

መስመር 3 = አዲሱ ስልት ጠቀሜታ አለው፤ ስልቱን ከተማሩ በኋላ ውጤታቸው ከፍ ብሏል።

በዚህ ማነፃፀሪያ የተገኘው የመጨረሻ ውጤት አስተማማኝነቱ 't-test' በተባለው ስታትስቲካዊ የስሌት ዘዴ ተለክቶ ድምዳሜ ላይ ተደርሷል።

# ምእራፍ 4. የማርኛ መደብ፣ ጾትና ቁጥር አመልካች ቅጥያ ምዕስደችን ማስተማሪያ ስልት (ቅመስ)

የማርኛ ምዕላደችን በ2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ለመማርና ለማስተማር የሚያስችል ብልሃት በማርኛ መርሐ-ትምህርቶች ውስጥ አለመኖር የዚህ ጥናት መነሻ እንደሆነ በምእራፍ 1 ተገልጿል። ችግሩን በተወሰነ ደረጃ (ከመደብ፣ ከጾትና ከቁጥር አኳያ) ለመቅረፍ ያግዝ ይሆናል በሚል የተቀየሰ አንድ ስልት ቀጥሎ ቀርቧል።

## 4.1. ማብራሪያ

"ቅመስ" በዚህ ጥናት የቀረበ የቅጥያ መለያ ስልት ነው። ስልቱ ሦስት ዋና ዋና ሃሳቦች አሉት። እነሱም "ተፈላጊ ቃል"፣ "መሰል ተቃራኒ" ና "አፎአ" የሚሉ ናቸው። በስልቱ ለመገልገል እነዚህን ሦስት ቁልፍ ሃሳቦች በደንብ መረዳት ያስፈልጋል።

"መሰል ተቃራኒ" ማለት ለተፈላጊው ቃል እንደሁኔታው የጾት፣ ወይም የመደብ፣ ወይም የቁጥር ወይም የሙያ ተቃራኒው የሆነ ቃል ማለት ነው። ለምሳሌ "ልጆች" ለሚለው ቃል መሰል ተቃራኒው "ልጅ" የሚለው ቃል ይሆናል። "ልጇቱ" በሚለው ቃል ውስጥ እንስታይ ጾት አመልካቹን ምዕላድ ለማውጣት ቢፈለግ ደግሞ፣ መሰል ተቃራኒው "ልጁ" የሚለው ቃል ነው ማለት ነው። በዚህ

መልክ ተፈላጊውን ቃል በሌሎች ሁኔታዎች (በመሠረታዊ ፍቺና በቅርጽ) ተመሳስሎ፣ በጸት፣ ወይም በቁጥር፣ ወይም በመደብ፣ ወይም በሙያ የሚቃረነው ቃል፣ መሰል ተቃራኒ ቃል ይባላል።

"አፎአ" ማለት ደግሞ ያማርኛ ፎኒማዊ አፃፃፍ ማለት ነው። ይህ አፃፃፍ አዲስ ሳይሆን ቀደም ሲልም በከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ይሠራበታል። አንድ ድምፅ በንድ ቅርጽ ተወክሎ አናባቢና ተነባቢ ተነጣጥለው እየተቀናጁ የሚፃፍበት ዘዴ ነው። የ"ቅመስ" መርሀ በዚህ አፃፃፍ ላይ የተመሠረተ በመሆኑ የተግባር መመሪያው ቀጥሎ ቀርቧል። በአፎአ ለመፃፍ ይህን መመሪያ መከተል ይገባል፤

1. ከሀ እስከ ፐ ላሉት ያማርኛ ተነባቢ ድምጾች የሳድስ ፊደሎቻቸውን ብቻ መውሰድ፤ ከ"በ" ዘር "ብ" ብቻ ይያዝና ሌሎች ስድስቱ ይቀራሉ። ከ"ተ" ዘርም "ት" ብቻ ተይዞ ሌሎቹ ይቀራሉ፤ ለሁሉም ተነባቢዎች እንደሁ ይደረጋል፤

2. ኧ፣ ኡ፣ ኢ፣ ኣ፣ ኤ፣ እ የሚሉትን የሰባቱን አናባቢዎች ፊደላት ሁሉንም መውሰድ፤

3. ተነባቢውንና አናባቢውን እያቀናጁ መፃፍ።

"በ" ለማለት "ብኧ"፣ "ቡ" ለማለት "ብኡ"፣ "ልጆች" ለማለት "ልእጆእች" እየተባለ ይፃፋል ማለት

ነው። ሲነበብ ተነባቢው ከናባቢው ጋር እንጂ ብቻውን አይጠራም። በአፎአ አፃፃፍ የሰድሱ አናባቢ በቃል መጨረሻ ላይ ሲመጣ በመደበኛው ድምፀት ድምፅ ስለሌለው አይፃፍም። በቃል መከከከልም በማይሰማበት ቦታ ላይ አይፃፍም። ለምሳሌ "ምርት" በሚለው ቃል ውስጥ ቀለም ያለው (ም) ለሚለው ተነባቢ ብቻ ነው። ከ(ር) ና ከ(ት) ጋር የ(እ) ድምፅ አይሰማም። በማይሰማበት ቦታ ላይ (እ) አይፃፍም።

<u>ተፈላጊ ቃል</u>፣ መለል <u>ተቃራኒ</u> እና <u>አፎአ</u> የሚሉት ሃሳቦች ግልጽ ከሆኑ የቅመስ መርህ ይቀርባል።

## 4.2. <u>የቅመስ መርሀ</u>

ተፈላጊውን ቃል ከላይ፣ መለል ተቃራኒውን ከታች አድርገው በሀ/ሰ መልክ ከስቀመጡ በኋላ ሁለቱን ቃላት በአፎአ ይፃፏቸውና ተመሳሳይ ፊደላትን አጣፍተው የለይኛውን ቀሪ እንደ መልስ ይውሰዱ።

ይህ መርህ የያዛቸውን ሃሳቦች እንደሚከተለው ዝርዝር አድርጎ በሦስት ህግጋት ማቅረብ ይቻላል፤

ህግ 1. ተፈላጊውን ቃል ከላይ፣ መለል ተቃራኒውን ከታች በሀ/ሰ መልክ ያስቀምጡ፣

ህግ 2. በሀ/ሰ ያስቀመጧቸውን ቃላት በአፎአ ይፃፏቸው

ህግ 3. ተመሳሳይ ፊደሎችን ያጣፉ፤ የለይኛው ቀሪ መልስዎ (የሚፈልጉት ምዕለድ) ነው።

ምሳሌ 1፡- "ልጆች" ከሚለው ቃል ውስጥ ብዛት አመልካቹን ምዕለድ ማግኘት ቢፈለግ፤

ሀ. ልጆች (ህግ 1)
ልጅ

ለ. ልእጅእች (ህግ 2)
ልእጅ

ሐ. ~~ልእጅእች~~= -እች (ህግ 3)
~~ልእጅ~~

የተገኘውን መልስ በምዕለድ ምልክት ውስጥ ማስቀመጥ፤ -እች። ጊዜ ለመቆጠብ ሲፈለግ የአሰራር ሂደቱን መዘርዘር አያሻም።

ምሳሌ 2፡- ልጅቱ ከሚለው ቃል ውስጥ እንስታይ ጾት አመልካቹን ምእለድ ለይቶ ለማውጣት ቢፈለግ፤

~~ልእጅኢትኡ~~ =/ኢት/
~~ልእጅኡ~~

<u>ምሳሌ 3</u>፦ "ሰበረልን" ከሚለው ቃል ውስጥ ባለቤት
አመልካቹን ምእላድ መለየት ቢፈለግ፤

<u>ስእብኧርኢልእን</u> =/-ኢ-/
ስእብኧርልእን

## 4.3. <u>ሊያጋጥሙ የሚችሉ ችግሮችና መፍትሔዎቻቸው</u>

ሀ. ተፈላጊው ቃልና መሰል ተቃራኒው ቃል ተጣፍተው የሚገኘው ቀሪ በክፍልፋይ መልክ ከሆነ የላይኛውን ቀሪ መልስ አድርገው ይውሰዱ፤ የታችኛውን ይተውት።

<u>ምሳሌ 4</u>፦ <u>ትመጣለች</u> ከሚለው ቃል ውስጥ መደብ ወይም ባለቤት አመልካቹን ምዕላድ ማግኘት ቢፈለግ፤

| | | |
|---|---|---|
| <u>ትመጣለች</u>= | <u>ትእምኧጥኣልኧች</u> = | <u>ት-ኧች</u>=/ት-ኧች/ |
| ይመጣል | ይእምኧጥኣል | ይ |

ለ. ተቀራራቢነት ያላቸው የድድና የላንቃ ድምጾች ሲያጋጥሙዎ ያጣፏቸው።

<u>ምሳሌ 5</u>፦ <u>ውሰጂ</u> ከሚለው ቃል ውሰጥ እንስታይ ጾት አመልካቹን ምዕላድ ማግኘት ቢፈለግ፤

| | | | |
|---|---|---|---|
| <u>ውሰጂ</u> | -<u>ውእስኧጅኢ</u> = | <u>ጅኢ</u> | =/-<u>ኢ</u>/ |
| ውሰድ | ውእስኧድ | ድ | |

ሐ. ተሰቢ አመልካች ምዕላድ ለማግኘት ሲፈለግ ቃሉን ተሰቢ አልባ በማድረግ መሰል ተቃራኒውን ማግኘት ይቻላል።

| | | | |
|---|---|---|---|
| <u>ምሳሌ 6</u> | ሀ.<u>ሰበርኩት</u> | =ለ.<u>ገደልከው</u> | ሐ.<u>ገደለቻቸው</u> |
| | ሰበርኩ | ገደልክ | ገደለች |

መ. ባለቤት ወይም መደብ አመልካች ምዕላዶችን ለማግኘት ሲፈለግ የሚከተሉትን ተጨማሪ ህግጋት መከተል ይጠቅማል።

1/ የ1ኛ መደብ ብዙ ቁጥር አመልካች ምዕላድ ሲፈለግ መሰል ተቃራኒውን 3ኛ መደብ ነጠላ ቁጥር ተበእታይ ጾት ያድርጉ፤

| | | | |
|---|---|---|---|
| <u>ምሳሌ 7</u> | ሀ.<u>ሰበርናቸው</u> | ለ.<u>እንሰብረዋለን</u> | ሐ.<u>እንሰበራት</u> |
| | ሰበራቸው | ይሰብረዋል | ይሰበራት |

2/1ኛ መደብ፣ነጠላ ቁጥር ሲፈለግ ቃሉ ተሰቢ ከሌለው መሰል ተቃራኒውን 3ኛ መደብ፣ ተበእታይ ጾት ማድረግ።

| | | | |
|---|---|---|---|
| <u>ምሳሌ 8</u> | ሀ.<u>ሰበርኩ</u> | ለ.<u>ሰብሬአለሁ</u> | ሐ.<u>እሰብራለሁ</u> |
| | ሰበረ | ሰብሯል | ይሰብራል |

ቃሉ ታሳቢ ካሰው መሰል ተቃራኒውን 3ኛ መደብ ብዙ ቁጥር አድርጎ [-ኡ]ን አስማጣፋት።

ምሳሌ 9፡ ሀ.ሰበርኩት ለ.ሰጠኋቸው ሐ.ልፃፍላቸው
ሰበሩት ሰጧቸው ይፃፉላቸው

3/2ኛ. መደብ፣ ብዙ ቁጥር ሲፈለግ መሰል ተቃራኒውን 3ኛ መደብ ብዙ ቁጥር ማድረግና በትእዛዝ አንቀጽ ላይ [ኡ]ን አስማጣፋት፤

ምሳሌ10፡ ሀ.ሰበራችሁ ለ.ትሰብራላችሁ ሐ.ስበሩ
ሰበሩ ይሰብራሉ ይስበሩ

4/2ኛ. መደብ ተባእታይ ጾት አመልካች ምዕላድ ሲፈለግ መሰል ተቃራኒውን ቃል 3ኛ መደብ ተባእታይ ማድረግ፤

ምሳሌ11፡ ሀ.ሰበርክ ለ.ትሰብራለህ ሐ.ስበር
ሰበረ ይሰብራል ይስበር

5/2ኛ መደብ አንስታይ ጾት አመልካች ምዕላድ ሲፈለግ፣ ግሱ ያሁን ጊዜ ካልሆነ፣ መሰል ተቃራኒውን 2ኛ መደብ ተባእታይ ማድረግ።

ምሳሌ 12፡ ሀ.ሰበርሽ ለ.ስበሪ ሐ.ሰብረሽል
ሰበርክ ስበር ሰብረሃል

ግሱ ያሁን ወይም የትንቢት ጊዜ ከሆነ ግን መሰል ተቃራኒውን 3ኛ መደብ ተበእታይ ማድረግ፤

ምሳሌ13:- ሀ.ትሰብሪያለሽ ለ.ትማሪያለሽ ሐ.ታነቢያለሽ
ይሰብራል ይማራል ያነባል

6/3ኛ.መደብ፣እንስታይ ጾት አመልካች ምዕላድ ሲፈለግ መሰል፤ ተቃራኒውን3ኛ መደብ ተበእታይ ማድረግ፤

ምሳሌ 14:- ሀ/ሰበረች ለ/ትሰብራለች ሐ/ትስበር
ሰበረ ይሰብራል ይስበር

7.3ኛ መደብ ብዙ ቁጥርና ያክብሮት አመልካች ምዕላድ ማግኘት ሲፈለግ መሰል ተቃራኒውን 2ኛ መደብ ብዙ ቁጥር ማድረግና በትእዛዝ አንቀጽ ላይ [ኡ]ን አለማጣፋት።

ምሳሌ 15- ሀ/ሰበሩ ለ/ይሰብራሉ ሐ/ይስበሩ
ሰበራችሁ ትሰብራለችሁ ስበሩ

## 4.4 የመረጃ ትንተና

### 4.4.1 የመረጃው አመደደብ

በምእራፍ 3 እንደተገለፀው ለስድስት ተከታታይ ሰምንታት ለተጠኚ ተማሪዎች በተሰጡ ፈተናዎች የጥናቱ መረጃ ተሰብስቧል። ፈተናዎቹ ፈ.1 ፈ.2 ፈ.3 ፈ.4 ፈ.5 ፈ.6

ተብለው ይታወቃሉ። በነዚህ ፈተናዎች አማካይነት የተሰበሰበው መረጃ፡ "ቅመመ" (ቅድመ-መመዘኛ መረጃ) ና "ድመመ" ድኅረ-መመዘኛ መረጃ ተብሎ በሁለት ተመድቧል። ቅመመ ያቀፈው ፈ1ን፣ ፈ2ንና ፈ3ን ሲሆን ድመመ ደግሞ ፈ4ን፣ ፈ5ንና ፈ6ን ይዟል።

**ቅመመ፣ ተጠኚ ተማሪዎች በዚህ ጥናት የቀረበውን የቅጥያ ምእላዳት መተንተኛ ስልት ከማወቃቸው በፊት ቁጥር፣ መደብና ጾታ አመልካች ቅጥያ ምእላዶችን ከቃል ላይ የመለየት ችሎታቸውን ሲያሳይ፣ ድመመ ደግሞ ተማሪዎቹ የተዘጋጀውን የቅጥያ ምእላዳት መተንተኛ ስልት ከተማሩ በኋላ ቁጥር፣ መደብና ጾታ አመልካች ቅጥያ ምዕላዶችን ከቃል ላይ የመለየት ችሎታቸውን ያመለክታል። ሁለቱም (ቅመመና ድመመ) በጥናቱ የተተኮረባቸውን ቅጥያ ምዕላዶች ከመረዳትና ከመተንተን አኳያ የተጠኚዎችን** ችሎታ የሚጠቁሙ መረጃዎች ናቸው። በቅመመና በድመመ መካከል ያለው ልዩነት በዚህ ጥናት የመነጨው ቅመስ (የቅጥያ መለያ ስልት) ነው። የተጠኚዎቹን የቅጥያ ምዕላድ ትንተና ችሎታ ሀ ብንለውና ቅመስን ደግሞ "ለ" ብንለው የሁለቱ መረጃዎች ልዩነት በሚከተለው ቀመር በቀላሉ ሊገለጽ ይችላል፤

ቅመመ = ሀ

ድመመ = ሀ+ለ


የ"ለ" መኖርና አለመኖር ሁለቱን መረጃዎች ይለያቸዋል።

በዚህ ንዑስ ምዕራፍ የምናየውና የምንተነትነው ይህን ልዩነት ይሆናል። ቅመመንና ድመመን በማነፃፀር የስነ ንኬት (effect) ለማግኘት ይሞከራል። በዚህም የጥናቱን መስምት ለመደገፍ ወይም ለመጣል ይቻልና ድምዳሜ ላይ ይደረሰል።

#### 4.4.4. የመረጃው አጠቃለይ መልክ

በየፈተናዎቹ የተገኘው ውጤት ድምር በግራፍ መልክ ሲቀርብ የሚከተለውን ይመስላል፤

**ግራፍ 2 የቅመመና የድመመ አጠቃለይ መልክ**





ግራፍ 2 በቅመመና በድመመ መካከል ልዩነት መኖሩን በጥቅሉ ይጠቁማል። ይሁን እንጂ ድምዳሜ ላይ ለመድረስ የሚያስችል ማስረጃ አይሰጥም (ሃቸና ፋርሃዲ ይ፤ 1982:53)። ቀጥሎ የቀረቡት ሠሌዳዎች የተሸለ ግነዘቤ ለማግኘት ይረዱ ይሆናል።

በዚህ ንዑስ ምዕራፍ የምናየውና የምንተነትነው ይህን ልዩነት ይሆናል። ቅመመንና ድመመን በማነፃፀር የስን ንኬት (effect) ለማግኘት ይሞክራል። በዚህም የጥናቱን መላምት ለመደገፍ ወይም ለመጣል ይቻልና ድምዳሜ ላይ ይደረሰል።

### 4.4.4. የመረጃው አጠቃለይ መልክ

በየፈተናዎቹ የተገኘው ውጤት ድምር በግራፍ መልክ ሲቀርብ የሚከተለውን ይመስላል፤

ግራፍ 2 የቅመመና የድመመ አጠቃለይ መልክ




ግራፍ 2 በቅመመና በድመመ መካከል ልዩነት መኖሩን በጥቅሉ ይጠቁማል። ይሁን እንጂ ድምዳሜ ላይ ለመድረስ የሚያስችል ማስረጃ አይሰጥም (ሃቻና ፋርሃዲ ይ፤ 1982:53)። ቀጥሎ የቀረቡት ሠሌዳዎች የተሻለ ግንዛቤ ለማግኘት ይረዱ ይሆናል።

### 4.4.3 የቅመመና የድመመ ንጽጽር

ሠሌዳ 3. የቅመመና የድመመ መጠነ-ተማከሎ (measure central tendancy) ንጽጽር

| ውጤት | ቅ | መ | መ | ድ | መ | መ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ከ10 | ፈ1 | ፈ2 | ፈ3 | ፈ4 | ፈ5 | ፈ6 |
| ተዘውታሪ | 2 | 2 | 2 | 8 | 10 | 10 |
| አማካይ ውጤት | 2.18 | 2.48 | 2.56 | 7.29 | 7.47 | 7.47 |


በሠሌዳ 3 እንደሚታየው በቅድመ-ፈተናዎች ያብዛኞቹ ተጠኚ ተማሪዎች ውጤት 2 ከ10 ሲሆን አማካይ ውጤታቸው ደግሞ ከ3 በታች ነው። በድኅረ-ፈተናዎች ግን አብዘኞቹ ተማሪዎች 8 ና 10 ከ10 ሲያገኙ አማካይ ውጤታቸው ከ7 በላይና ከ8 በታች ሆኗል። ይህም ተጠኚዎቹ ከቅድመ-ፈተናዎች ይልቅ በድኅረ-ፈተናዎች የተሻለ ውጤት እንደመጡ ያመለክታል። ቢሆንም በዚህ ንጽጽር ብቻ ርግጠኛ መሆን ስለማይቻል የድግግሞሽና ያንፃራዊ ድግግሞሽ ንጽጽር ማድረግ ያስፈልጋል (ሃቸና ፋርሃዲ,ይ፤ 1982)።

ከገጽ 63ና64 መረዳት እንደሚቻለው በቅድመ ፈተናዎች የተገኘው ከፍተኛ ውጤት 5 ከ10 ሲሆን በድኅረ ፈተናዎች የተገኘው ከፍተኛ ውጤት 10 ከ10 ነው። በቅድመ-ፈተናዎች የተገኘው ከፍተኛው የውጤት ድግግሞሽና አንፃራዊ

ድግግሞሽ ዝቅተኛ ሆኗል። በዚህም በቅመመና ድመመ መከከል ጎላ ያለ ልዩነት ታይቷል።

ከዚህም በላይ በተደረጉት የንጽጽር ዘዴዎች፣ "ለ" ማለትም በዚህ ጥናት የቀረበው የቅጥያ መለያ ስልት ውጤታማ ንኬት ይኖረዋል ብሎ ለመገመት የሚያስችል ሁኔታ የሚታይ ይመስላል። ሆኖም ድምዳሜ ላይ ከመደረሱ በፊት ለጥናቱ በተመረጠው መሣሪያ አማካይነት የሚደረገው ንጽጽር መታየት ይኖርበታል። በምእራፍ 3 እንደተገለፀው ለጥናቱ የተመረጠው መሣሪያ የራሱ የውጤት ማነፃፀሪያ ዘዴ አለው። በቅድመ-ፈተናዎቹና በድኅረ-ፈተናዎቹ የተገኘው መረጃ በገጽ 40 ከቀረቡት የ'Time series design' የማነፃፀሪያ መስመሮች የትኛውን እንደሚያስገኝ ቀጥሎ በግራፍ 3 ይታያል።

ግራፍ 3. የቅመመና የድመመ ንጽጽር በ'Time series Design' የንጽጽር ዘዴ



በግራፍ 3 ንጽጽሩ የቀረበው በየፈናዎቹ እያንዳንዱ ተጠኚ ተማሪ ያገኘው ውጤት ተደምሮና በ100 ተከፍሎ በተገኘው ቁጥር አማካይነት በተነደፈ የግራፍ መስመር ነው። የተገኘው መስመር በቅድመ-ፈተናዎች ዝቅ ያለ ሆኖ በድኅረ-ፈተናዎች ወደ ላይ ያቀና ነው። በቅመመ ከ2 በታች ያሉ ነጥቦችን ሲያመለክት፣ በድመመ ከ5 በላይ ያሉ ነጥቦችን ያሳያል። ይህ መስመር በገጽ 40 ከቀረቡት የጥናቱ ማነፃፀሪያ ሞዴል መስመሮች ሦስተኛውን መስመር መስሏል። የመስመር ሦስት ዓይነተኛ ጠባይ በቅድመ-ፈተናዎች ወደታች ዝቅ ያለ ሆኖ በድኅረ-ፈተናዎች ወደላይ የተነሳ መሆኑ ነው። በዚህ ጥናት የተገኘውም መስመር ይህን ጠባይ ጠቊሟል። ይህ ሁኔታ ከጥናቱ መላምት ጋር የሚቃረን ውጤት መገኘቱን ያመለክታል። ይሁን እንጂ መላምቱን ውድቅ አድርጎ አማራጩን ለመያዝ የስታትስቲካዊ ስሌት ማረጋገጫ ያስፈልጋል። ስለዚህ መላምቱን የመደገፊያው ነጥብ ከ05 የሚያንስ ውጤት መገኘት ሆኖ $t = \sqrt{\frac{S^2 \bar{D}}{n}}$ በሚለው ቀመር አማካይነት የተከሄደው እስታትስቲካዊ ስሌት ውጤቱ እንደሚከተለው ቀርቧል፤

ሠሌዳ 4 በድመመና በቅመመ ልዩነት (ስ) ላይ የT ዋጋ

| ድመመ-ቅመመ ="ስ"(ልዩነት) | በስታትስቲካዊ ስሌት"የተገኘው"ለ" (T-observed) | በስታትስቲካዊ ስሌትየ"ለ" ዋጋ (T-value) |
|---|---|---|
| ስ1(ፈ4-ፈ1) | 22.2 | 1.67 |

| | | |
|---|---|---|
| ስ2(ፈ5-ፈ2) | 19.69 | 1.67 |
| ስ3(ፈ6-ፈ3) | 18.48 | 1.67 |
| ስ4(አማካይ2-አማካይ1) | 19.8 | 1.67 |

የα05 ዋጋ 1.67 ሆኖ ሳለ የተገኘው ውጤት ከዚህ በጣም የሚበልጥ ሆኗል። በመሆኑም መላምቱ በስታትስቲካዊ መረጃ የሚደገፍ አልሆነም። ስለዚህ የቀረበው የቅጥያ መለያ ስልት ለተማሪዎች ጠቀሜታ አለው የሚለው አማራጭ መላምት ተቀባይነት አግኝቷል።

# ምዕራፍ 5. ጭምቅ ሃሰብ (Summary)፣ ማጠቃለያ (Cocniusion) እናጠቃሚ አስተያየት (Recommendation)

## 5.0 አጭር መግቢያ

ይህ ምእራፍ የጥናቱ የመጨረሻ ክፍል በመሆኑ፣ ባለፉት ምእራፎች የተነሱ አበይት ነጥበች አንድ ላይ የሚዘመዱበት፣ የሚጠቃለሉበትና ትርጊሜ አግኝተው የሚቋጩበት ይሆናል።

## 5.1 ጭምቅ ሃሰብ

የጥናቱ ዓለማ፦ ባማርኛ ቋንቋ በመደበኛውና በዘሬው አውድ መደብ፣ ጾትና ቁጥር አመልካች የሆኑ ኢቃል ለዋጭ ቅጥያ ምእለደችን በ2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውስጥ በተሸለ መንገድ ለማስተማር የሚቻልበትን ብልሃት ማመንጨት መሆኑ በምእራፍ 1 ተገልጿል። ይህን ዓለማ ማንሳት ያስፈለገበት ምክንያት ምእለደችን ከቃል ላይ ለይቶ ለመረዳት የ2ኛ ደረጃ ተማሪዎች ችግር ያለባቸው መሆኑ ከመስክ በመታየቱና በናሙና [illegible] ጥናትም በመጨበጡ ነው።

ችግሩ የሚቀረፍበትን ብልሃት ለማመንጨት በተደረገው ሙከራ "ቅመስ" የሚል አንድ የቅጥያ ምዕለደት ማስተማሪያ ስልት ተቀይሶ ውጤታማ ሊሆን መቻል አለመቻሉን

ለመተንበይ በ73 የ10ኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ ጥናት ተደርጓል። ጥናቱ የተመሰረተው ሃቼና ፋርሃዲይ (1982) እንዲሁም ሴሊገርና ሾሃሚ (1989) ባረጋገጡት መሠረት፣ በመማሪያ ክፍል ውስጥ ለሚደረግ የቋንቋ ጥናት ይበልጥ ተመራጭነትና አስተማማኝነት አለው ተብሎ በሚገመተው "ከፊል ፍትነታዊ" (Quasi-Experimental Design) በተባለው ያጠናን ዘዴ ላይ ሲሆን መረጃ የተሰበሰበውም በፈተናዎች ነው።

ፈተናዎች "የተሻሉ የመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያዎች" ናቸው ቢባልም ፋይዳ የሚኖራቸው 'ግብመቺነት' /Validity/ እና 'አስተማማኝነት' /Reliability/ ሲኖራቸው በመሆኑ በዚህ ረገድም የሚከተሉትን ጥንቃቄዎች ለማድረግ ተሞክሯል።

ሀ. ግብመቺነትን በተመለከተ

ደጀኔ (1990:64)፣ ክርማነስና ዜለር (1985:17) ን ጠቅሰው የግብመቺነት /Validity/ን ትርጉምሰን (definition) እንደሚከተለው አቅርበዋል፤

> Validity is the extent to which any measuring instrument measures what is intended to measure.

በዚህ ጥናት በፈተናዎቹ አማካይነት ሊታወቅ የሚፈለግ አንድ ውሱን ባሕሪ አለ፤ ይኸውም ተጠኚዎቹ አዲሱን

የቅመስ መርህ ከማወቃቸው በፊትና በኋላ ከማርኛ ቃላት ላይ መደብ፣ ጾትና ቁጥር አመልካች የሆኑ ቅጥያ ምእላዶችን ለይቶ የመረዳት ችሎታቸው ምን ያህል እንደሆነ ነው። የተዘጋጁት ፈተናዎች ይህን ተፈላጊ በሕሪ በተከከል በመለከት ግብ መምታት ይጠበቅባቸዋል። ፈተናዎቹ ይህን ግብ ከስገኙ፣ ከላይ በቀረበው ትርጉሞ ሰን መሠረት ግብመቺ ናቸው ይበሳል። ግቡ ካልተገኘ ግን ፈተናዎቹ ግብሰቸ መሆናቸው ነው። እዚህ ላይ የሚነሰው ጥያቄ ያንድ ፈተና ግብ መቺነት ወይም ሰቺነት እንዴት ይረጋገጣል? የሚለው ነው። ይህ ቁልፍ ጥያቄ ከግብ መቺነት /Validity/ ዓይነቶች በሕሪ አኳያ የሚታይ ይሆናል።

ደጀኔ (1990:64-5) ከባለሙያዎች በመጥቀስ እንደገለፁት ዋና ዋናዎቹ የግብመቺነት ዓይነቶች ፦ 'አፍአዊ ግብመቺነት' (Face validity)፣ 'ይዘታዊ' ግብመቺነት (Content validity) 'ተዛምዶአዊ ግብመቺነት' (Concurent validity)፣ 'የትንበያ ግብመቺነት' (Predictive validity) እና ገንቢ ግብመቸነት' (Construct validity) ናቸው።

<u>አፍአዊ ግብመቺነት</u>፣ የአስተያየት ጉዳይ ነው፤ ተፈታኞቹን ስለፈተናው በመጠየቅ ሊጨበጥ ይችላል። በዚህ ረገድ በዚህ ጥናት የተዘጋጁት ፈተናዎች በሥራ ላይ ከመዋላቸው በፊት፣ ናሙና ጥናት (Pilot study) ተደርጎና ከተማሪዎች አስተያየት ተወስደ ማሻሻያ ተደርጎባቸዋል።

<u>ይዘታዊ ግብመቺነት</u>፣ ፈተናው እንዲመዝን በሚፈለገው

ነገር ላይ አጥጋቢ የይዘት ወከይነትና የስርጭት አጠቃላይነት ያለው መሆን አለመሆኑ የሚታይበት ነው። በዚህ ጥናት ለቀረቡት ፈተናዎች ይዘት የሆኑት መደብ፣ ጾትና ቁጥር አመልካች ቅጥያ ምእላዶች ናቸው።እነዚህ ምእላዶች በቋንቋው ውስጥ ቁጥራቸው ውሱን በመሆኑ ይዘታዊ ግብመቺነት ያለው ፈተና ለማዘጋጀት ችግር አላጋጠመም። በምዕራፍ 3 እንደተገለፀውና በአባሪ 1 ላይም እንደሚታየው በየፈተናዎቹ በይዘትነት የቀረቡት ምእላዶች፣ /-ዎች፣ -ኦች፣ እኑ፣ -አን፣ -አት፣-ኡ፣-ኢ፣-ሽ፣-ች/ የሚሉት ናቸው። እነዚህ ቅጥያ ምእላዶች፣ በይዘትና በስርጭት መደብ፣ ጾትና ቁጥር አመልካች ሲሆኑ ለየምድቡ በቂ ውክልና ያላቸውና አንዳንድ ቦታ ላይም (ለምሳሌ ያማርኛ አብዢዎችንና አንስታይ ጾት አመልካቾችን አስመልክቶ) 100% የቀረቡ ናቸው።

<u>ተዛምዶአዊ ግብመቺነት</u>፣ ፈተናው እንዲለካው ስለሚፈለገው ባሕሪ ከተፈታኞቹ ያስገኘው ውጤት በሌላ ፈተናም ሊገኝ የሚችል፣ ወይም ፈተናው ተደጋግሞ ቢሰጥ ውጤቱ የማይለዋወጥ ሊሆን የመቻሉ ሁኔታ ነው። ይህን ግብ ለማስገኘት ሲባል በዚህ ጥናት የተዘጋጁት ፈተናዎች ምርጫ ከመሆናቸው ይልቅ በሙሉ መልስ የሚሞላባቸው ጥያቄዎች ሆነዋል። ይህ የተደረገው በባለምርጫ ጥያቄዎች ላይ ትክክለኛው መልስ ባይሰጡኝም ሊገኝ ሲችል በባለባዶ ቦታ ጥያቄዎች ላይ ግን ትክክለኛው መልስ ሊገኝ የሚችለው ያለምንም አማራጭ በተፈታኝ ችሎታ ብቻ ይሆናል በሚል እምነት ነው። በይዘት አንድ ሆነው በቅርጽ ብቻ የሚለያዩ

ስድስት ፈተናዎች ከዲሱ ስልት በፊትና በኋላ ተሰጥተው የተገኘው ውጤት በየምድቡ ተመሳሳይና ተቀራራቢ ሆኗል፤ (አባሪ ፯ን ይመለከቷል)።

<u>የትንበያ ግብመቼነት</u>፣ ተፈላጊነቱ በተወሰነ ጉዳይ ላይ ተጠኚው ወደፊት ሊኖረው የሚችለውን ባሕሪ ለመተንበይ ስለሆነ እናልፈዋለን።

<u>ገንቢ ግብመቼነት</u>፣ ደግሞ አንድ ፈተና "ሊለካ የታለመበትን ችሎታ ብቻ የሚለካ" ሆኖ የመቀረፁ ጉዳይ ነው። ደጀኔ (1990:65) እንደገለፁት ይህ ጉዳይ "በጣም አስፈላጊ"ና የዚያኑ ያህል ደግሞ "በጣም ውስብስብ" በመሆኑ ማረጋገጫው ይህ ነው ለማለት ያስቸግራል። በጠቃላይ መልኩ ግን የፈተናዎቹ አቀራረፅ፣ ውስብስብነትና አደናጋሪነት ሳይኖረው የሚፈለገውን ጉዳይ ብቻ በቀጥታና በግልጽ የሚጠይቅ ይሆናል የሚል እምነት አለ። የሚከተሉት ከፈተናው የተቀነጨቡ ናሙናዎች ናቸው።

ፈተና 1 ጥያቄ 4 "ከቢዎች" በሚለው ቃል ውስጥ ብዙ ቁጥር

አመልካቹ ቅጥያ ________________ ነው።

ፈተና 2 ጥያቄ 1. "ደብተር" ብሎ "ደብተሮች" ቢል ብዛት

አመልካቹ ቅጥያ ________________ ነው።

ፈተና 3. ጥያቄ 3. "ልዑል" ብሎ "ልዑላን" ቢል ብዛት

ለማመልከት የተጨመረው ቅጥያ................... ነው።

ፈተና 4. ጥያቄ 10. "ተቆጣጠር" ለወንድ ሲሆን "ተቆጣጠሪ" ለሴት ነው፤ በሁለተኛው ቃል ውስጥ ሴቴ ጾታ የሚያመለክተው ቅጥያ ________________ ነው።

ፈተና 5. ጥየቄ 9."አስጠንቅቅ" ብሎ "አስጠንቅቂ" ሲል ሴቴ ጾታ የሚያመለክተው ቅጥያ ______________ ነው።

ፈተና 6. ጥያቄ 8. "ሰማእት" ብሎ "ሰማእታት" ቢል ብዙ ቁጥር አመልካቾ ቅጥያ ______________ ነው።

## ለ. <u>አስተማማኝነትን በተመለከተ</u>

አስተማማኝነትን ደጀኔ (1990:65) ባለሙያዎች በመጥቀስ፤ Reliability is the degree to which a test consistently measures whatever it measures. በማለት ገልፀውታል።

ይህን ግብ ለማስገኘት ይረዳል በሚል ከፊል ፍትነታዊ የተባለው የጥናቱ ዘዴ ተመርጦ፤ በዘዴው ሞዴል መሠረት በየፈተናዎቹ መካከል የአንድ ሳምንት የጊዜ ልዩነት እየተደረገ ሦስት ቅድመ-ፈተናዎች (Pre-tests) እና ሦስት ድኅረ-ፈተናዎች (Post tests) ተሰጥተው ከጥኚው የተዘጋጁ መልሶችን በያዙና የመጀመሪያ ዲግሪ ባላቸው በሁለት መምህራን ፈተናዎቹ ታርመዋል። ከአባሪ 2 መረዳት እንደሚቻለው በሁለቱም ምድቦች በየፈተናዎቹ ተመሳሳይነትና ተቀራራቢነት ያለው ውጤት ተገኝቷል።

በሁለቱ ምድቦች ማለትም በቅድመ-ፈተናዎቹና

በድኅረ-ፈተናዎቹ መካከል ያለው የርስበርስ ተዛምዶና ልዩነት ብራውን (1983:50) እና ሄንክሌና ተባባሪዎቹ (1982:200) ባቀረቡት መሠረት በፔያርሰን የ'Correletion coefficient' የስሌት ዘዴ ተለክቶ የሚከተለው አጥጋቢ ውጤት ተገኝቷል።

ሠሌዳ 5 <u>የፈተናዎቹ የርስበርስ ተዛምዶ</u> <u>(Correletion coefficient)</u>

| | |
|---|---|
| rፈ1 ፈ2 = 0.8 | rፈ4 ፈ5 = 0.81 |
| rፈ1 ፈ3 = 0.58 | rፈ4 ፈ6 = 0.81 |
| rፈ2 ፈ3 = 0.78 | rፈ5 ፈ6 = 0.82 |

በዚህ መልክ ግብመቸነትና አስተማማኝነት እንዳላቸው በሚገመቱ ፈተናዎች የተወሰደው መረጃ ቅድመ-ስልት መረጃና ድኅረ-ስልት መረጃ በሚል በሁለት ተመድቦ፣ በምዕራፍ 4 እንደቀረበው በተለያዩ መንገዶች የንጽጽር ትንተና ከተካሄደበት በኋላ ሦስት ዋና ዋና ጉዳዮችን ያመለከተ ውጤት ተገኝቷል።

አንደኛ፣ ተጠኚ ተማሪዎቹ ለሦስት ሣምንታት በተከታታይ በወሰዷቸው ሦስት ቅድመ-ፈተናዎች ያስመዘገቡት ውጤት እጅግ በጣም ዝቅተኛ ሆኗል። 73 ተጠኚ ተማሪዎች ከ10

በታረሙት ሦስት ቅድመ ፈተናዎች ያገኙት ማርክ ድግግሞሹና አንፃራዊ ድግግሞሽ ይህን አመልክቷል።

ሠሌዳ ፩፦ በቅድመ ፈተናዎች የተገኘው ማርክ ድግሞሞሽና አንፃራዊ ድግግሞሽ

| | ፈ.1 | | ፈ.2 | | ፈ.3 | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | ድግ | አድግ | ድግ | አድግ | ድግ | አድግ |
| 10 | - | - | - | - | - | - |
| 9 | - | - | - | - | - | - |
| 8 | - | - | - | - | - | - |
| 7 | - | - | - | - | - | - |
| 6 | - | - | - | - | - | - |
| 5 | 4 | .06 | 3 | .04 | 3 | .04 |
| 4 | 6 | .08 | 5 | .07 | 6 | .08 |
| 3 | 9 | .12 | 18 | .25 | 24 | .33 |
| 2 | 37 | .51 | 41 | .56 | 36 | .49 |
| 1 | 14 | .19 | 6 | .08 | 4 | .06 |
| 0 | 3 | .04 | - | - | - | - |

መፍቻ፤ ድግ = ድግሞሞሽ፣ አድግ= አንፃራዊ ድግሞሞሽ።

በቅድመ ፈተናዎች የተገኘው ከፍተኛው ውጤት 50% ነው። ይህን ውጤት ያገኙ ተማሪዎችም በመጀመሪያው ፈተና 5.5%፣ በሁለተኛውና በሦስተኛው ፈተናዎች በያንዳንዱ 4% ናቸው። በሦስቱም ፈተናዎች አብዛኞቹ ተማሪዎች ያገኙት ውጤት

20% ነው። 955% ተማሪዎች ቅድመ ፈተናውን አላለፉም። በማርኛ ቋንቋ አፋቸውን ከልፈቱ ተጠኚዎች መከከል አንድ ተማሪ በፈተና 1 ላይ 50% ከማምጣቱ በስተቀር በቅድመ ፈተናዎች ያለፈ ተማሪ የለም።

ሁለተኛ፦ ተጠኚ ተማሪዎቹ ለሦስት ተከታታይ ሣምንታት በወሰዷቸው ሦስት ድኅረ-ፈተናዎች ያስመዘገቡት ውጤት በአንፃራዊ መልኩ በጣም ከፍተኛ ሆኗል። ድግግሞሹ እና አፃራዊ ድግግሞሹ ቀጥሎ ቀርቧል።

ሠሌዳ 7፦ <u>በድኅረ-ፈተናዎች የተገኘው ውጤት ድግግሞሽና አንፃራዊ ድግግሞሽ</u>

| | ፈ.4 | | ፈ.5 | | ፈ.6 | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ማርክ | ድግ | አድግ | ድግ | አድግ | ድግ | አድግ |
| 10 | 13 | .18 | 19 | .26 | 19 | .26 |
| 9 | 11 | .15 | 12 | .16 | 10 | .14 |
| 8 | 20 | .27 | 16 | .22 | 15 | .21 |
| 7 | 9 | .12 | 5 | .07 | 12 | .16 |
| 6 | 4 | .05 | 5 | .07 | 2 | .03 |
| 5 | 2 | .03 | 2 | .03 | 1 | .01 |
| 4 | 6 | .08 | 5 | .07 | 6 | .08 |
| 3 | 6 | .08 | 6 | .08 | 6 | .08 |
| 2 | 2 | .03 | 3 | .04 | 2 | .03 |
| 1 | - | - | - | - | - | - |
| 0 | - | - | - | - | - | - |

በድኅረ-ፈተናዎቹ ከፍተኛዎቹ የድግግሞሽ ማርከች 8 ከ10 እና 10 ከ10 ናቸው። 84.94% የሚሆኑ ተጠኚ ተማሪዎች ከ50% እስከ 100% ውጤት በማምጣት ድኅረ ፈተናዎቹን አልፈዋል። ድህረ ፈተናዎቹን ለማለፍ ያልቻሉት 15.06% ናቸው።

ሦስተኛ፡- በማርኛ አፋቸውን በፈቱና ባልፈቱ ተማሪዎች መከከል የጥናቱን ትኩረት አስመልክቶ የሚያጋጥም ሁኔታ ቢኖር ለማጤን በተደረገው ክትትል የሚከተለው ውጤት ተገኝቷል።

ከ73ቱ ተጠኚ ተማሪዎች ውስጥ 17ቱ በማርኛ አፋቸውን ያልፈቱ ሲሆኑ በማርኛ አፋቸውን የፈቱ ደግሞ 56 ነበሩ። በማርኛ አፋቸውን ካልፈቱ ተጠኚዎች ውስጥ ድህረ ፈተናውን ያለፉ በቁጥር 15፣ በመቶኛ 88.23% ሲሆኑ የወደቁ በቁጥር 2፣ በመቶኛ 11.76% ናቸው። በማርኛ አፋቸውን ከፈቱ 56 ተጠኚ ተማሪዎች ውስጥ ድኅረ-ፈተናውን ያለፉ 84% ሲሆኑ የወደቁ 16% ናቸው።

## 5.2. ማጠቃለያ

በ5.1 በተገለፀው መሠረት በዚህ ጥናት የተደረሰበት ግኝት የሚከተሉትን ሁኔታዎች ያመለክታል።

አንደኛ በቅድመ-ፈተናዎች የተገኘው በጣም ዝቅተኛ ውጤት ተማሪዎቹ ከቃል ላይ ቅጥያ ምዕላደችን ለመረደት የነሰ ችግር

ያሰባቸው መሆኑን ያሳያል። ይህ እውነታ በጥናቱ ውስጥ ከሌላ አቅጣጫም ተጨብጧል። በያንዳንዱ ፈተና ስር ከቀረቡት 10 ጥያቄዎች ውስጥ ሁለቱ ቅጥያቸው በግልጽ የሚታይ፣ ማለትም በማርኛው አፃፃፍ ያልተዋጠ እንዲሆን ሆን ተብሎ ተደርጎ ነበር፤ በፈተና 1. ጥያቄ 4. ላይ እንደቀረበው "ከበዎች" እንደሚለው ዓይነት ማለት ነው። አብዛኞቹ ተጠኚ ተማሪዎች እነዚህን ጥያቄዎች በትክክል ለመመለስ ችለዋል። በሦስቱም ቅድመ-ፈተናዎች ከፍተኛው ተደጋጋሚ ውጤት 2 የመሆኑ ምሥጢር ይህ ሳይሆን አይቀርም። ተጠኚዎቹ በማርኛው አፃፃፍ ሳይዋጥ በግልጽ የሚታየውን ቅጥያ ምእለድ ለይተው ለመገንዘብ ችለዋል። በአፃፃፍ የተዋጠውንና ከእይታ የተደበቀውን ምዕለድ ግን ለይተው ለማመልከት አልቻሉም።

ሁለተኛ በቅድመ-ፈተናዎቹ የተገኘው ከፍተኛ ውጤት ደግሞ ለችግሩ በመፍትሔነት የቀረበው ስልት ለተማሪዎቹ ጠቀሜታ ያለው መሆኑን ያመለክታል። ስልቱን ከተማሩ በኋላ ውጤታቸውን ያሳሻሉና ይብስ ዝቅተኛ ውጤት ያመጡ ተማሪዎች አልታጡም። ሆኖም እንዲህ ዓይነት ተማሪዎች ቁጥራቸው በጣም አነስተኛ (15.06%) በመሆኑ ስልቱ ፋይዳ አይኖረውም ብሎ ለመገመት በቂ መረጃ ባይሆኑም ሁሉም ተማሪዎች በስልቱ እኩል ተጠቃሚ የማይሆኑባቸው ሌሎች 'ምክኑታዎች' (Factors) ለመኖራቸው ፍንጭ ይሰጣሉ። እነዚህም ምክኑታዎች ምናልባት በተማሪዎቹ መካከል ያሉት ግለሰባዊ ልዩነቶች ሊሆኑ ይችላሉ። ተማሪዎች፣ በእድሜ፣ በብልኅነት (inteligence)፣ በቋንቋ ተሰጥኦ (aptitude)፣ በአእምሮታዊ ስልት (Cognitive style)፣ በመቀስቅስ (Motivation) በሰብእና፣

በማኅበራዊ ደራዎችና በመሰሰለት እንደሚለያዩና እነዚህም ልዩነቶች በቋንቋ ትምህርት ላይ በጎ ወይም ጎጂ ንኬት ሊኖራቸው እንደሚችል ብራውን (1980)፣ ኤሊስ (1985)፣ እስፖልስኪ (1983)፣ እስተርን (1983) ታደሰ (1990) እና ሌሎችም ምሁራን ዘግበዋል።

ሦስተኛ፣ አፋቸውን ባማርኛ በፈቱና ባልፈቱ ተጠኚዎች መካከል የታየው ልዩነት አማርኛ 2ኛ ቋንቋቸው ለሆነ ተማሪዎች ችግሩ የበለጠ መሆኑንና ስለቱም ለነዚህ ተማሪዎች ብልሜ ያለው ጠቀሜታ የለጠ መሆኑን ይጠቁማል።

## 5.3 ጠቃሚ አስተያየት (Rcommendation)

ሥነ-ልሳን በ2ኛ ደረጃ ትምርት ቤቶች ውስጥ ካማርኛ የትምህርት ዓለማዎች አንዱ ሆኖ ከተቀረፀ፣ ትምህርቱ የሚተለለፍበት በቂ ብልሃትም አብሮ ሊቀርብ ይገባል። ፍሪማን (1987) እና ሸው (1987) በዚህ ጉዳይ ላይ የለነዘሩትን አስተያየት ደረጀ (1986:21) እንደሚከተለው ጠቅሰውታል፤

> በትምህርትነት የሚቀርቡትን የቋንቋ አከሎች እንዴት እንደሚከፋፈሉ፣ እያንዳንዱ ክፍፍል ለማስ ታማር በሚያመች መልክ እንዴት እንደሚዘጋጅና በትምህርትነት እንዴት እንደሚቀርብ አጣምሮ ማወቅ ያስፈልጋል። የሚቀርበውን የቋንቋ አካል (ለምሳሌ የድምፅ አወዳደቅና አነሳስ፣ ማጥበቅና ማላለት፣ ተገቢው ቃል በተገቢው ቦታ መቀጠም፣ ትክክለኛውን የሰዋሰው አጠቃቀም) እንዴት ወደ ተማሪዎቹ ማስተለለፍ

እንደሚቻልና ተማሪዎቹም በተቀላጠፈና በቀለለ ዘዴ እንዲለምዷቸው ማድረጊያውንም ስልት ማሳየት ያስፈልጋል።

ማስተማሪያ ስልቶች ተጨባጭ አካባቢያዊ ችግሮችን ለመፍታት የሚያስችሉ የክፍል ውስጥ መገልገያ መሣሪያዎች ናቸው (ሪቻርድስና ሮጀርስ፤ 1986:28)። ለአማርኛም በዚሁ መልክ የግል ችግሮቹን የሚፈታባቸው ማስተማሪያ ስልቶች ያስፈልጉታል። በተለይ የምዕላድ ማስተማሪያው ዘዴ በአማርኛ መርሐ ትምህርቶች ውስጥ ያለመታቀፉ ጉዳይ ቸል መባል የለበትም። በመጀመሪያ ደረጃ ችግሩ እውቅና ሊሰጠው ይገባል፤ ቀጥሎ መፍትሔ ሊፈለግለት ያሻል። መፍትሔው ከውጪ የሚጠበቅ ሳይሆን ከውስጥ የሚመነጭ ነው። በመሆኑም ዛሬ በዚህ ጥናት የተጀመረው ትልም ነገ በሌሎች ባለሙያዎች ተጠናክሮና ዳብሮ ሁነኛ መፍትሔ ያስገኝ ዘንድ ሁኔታዎችን ማመቻቸት ያስፈልጋል።

ስለዚህ በዚህ ጥናት የቀረበው ግኝት ጠቀሜታው በጥሩ ፍንጭ የታየ ስለሆነና ዘላቂ መፍትሔ ለማመንጨት ለሚደረገው ጠለቅ ያለ ምርምርም መነሻና አቅጣጫ አመልካች ሊሆን ስለሚችል በማርኛ መርሐ ትምህርቶች፣ በመማሪያ መጽሐፎችና በመምህራን ማስልጠኛ ተቋማት መርሐ-ግብሮች ውስጥ ተገቢ ቦታ ቢሰጠውና ቢሰራበት፣ እየተሰራበትም ቢሻሻልና ቢዳብር መልካም ይሆናል።

# ዋቢ መጻሕፍት


አለማየሁ ፀጋዬ። 1986። "በዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች ድርሰት ውስጥ የሚፈፀሙ ዋና ዋና የስህተት ምንጮች ትንተና"፤ የማስተርስ ዲግሪ ማሟያ። አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ።

አለማየሁ ሞገስ። 1957። የድርሰት አብነት። አዲስ አበባ። ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት።

ባዬ ይማም። 1987። የአማርኛ ሰዋሰው። አዲስ አበባ፤ ት.መ.ማ.ማ.ድ.

በአፀደ ህፃናትና መደበኛ ትምህርት ዋና ክፍል የአማርኛ ትምህ ርት ቡድን። 1984። የአሥረኛ ክፍል ያማርኛ መምሪያ። አዲስ አበባ፤ የትምህርት መሣሪያዎች ማምረቻና ማከፋፈያ ድርጅት።

---------------------------------------። 1985። የዘጠነኛ ክፍል ያማርኛ መምሪያ። አዲስ አበባ፤ የትምህርት መሣሪያዎች ማምረቻና ማከፋፈያ ድርጅት።

ደረጀ ገብሬ። 1986። "በከተቤ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ በዲፕሎማ መርሐ-ግብር የሚሰጡ አቢይ ያማርኛ ኮርሶች ይዘት ትንተናና ግምገማ፤ በቋንቋዎች ጥናት ተቋም አማርኛን በማስተማር ዘዴ ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት (ቴሲስ)"። አዲስ አበባ ዩንቨርስቲ።

ሃይሉ ፋሲስ። [illegible]። *ሥርዓታዊ ያማርኛ ሰዋሰው*። አዲስ አበባ ዩንቨርስቲ፤ ያልታተመ።

ኪዳነወልድ ክፍሌ። 1934። *መዝገበ ፊደላት ሌማውያት*።2ኛ መጽሐፍ፤ ሚሲዮን ማተሚያ ቤት፤ ድሬደዋ።

------------------------------------። 1948። *መጽሐፈ ሰዋሰው ወግስ ወመዝገበ ቃላት ሀዲስ*። አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፤ አዲስ አበባ።

መርስኤሃዘን ወልደቂርቆስ። 1957። *የአማርኛ ሰዋሰው*። አዲስ አበባ፤ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት።

ተክለማርያም ፋንታዬ። 1957። አንደኛ *ተግባራዊ መጽሐፈ*። አዲስ አበባ፤ ትምህርት ማተሚያ ቤት።

--------------------------------1957።*ሆህተ-ጥበብ ዘ ስነ-ጽሑፍ*። አዲስ አበባ፤ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት።

ጥሩነሽ በየነ። 1965። *ልበን*። አሥመራ፤ [illegible] ዘማኅበረ ጣዋሪያት ማተሚያ ቤት።

ይትባረክ ወልደሚካኤል። 1966። *ዘመናዊ ሰዋሰውና መ ገብተ፡ልሳን*። አዲስ አበባ፤ ትንሳኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት።

Alemayehu Haile. 1987. "An Autosegmental Approach to Amharic Intonation"; Ph.D. Thesis, University of London.

________.1990."An Autosegmental Approach to Some Amharic Declarative and Interc-gative contours"Proceedings of the 1st National conference of Ethiopian stu-dies.Addis Ababa Univeristy,(449-460).

________. 1991. "The Morphological Structure of the Imperative stem in Amharic",Ethiopian Journal of Education XII: 1(61-76).

Baye Yimam. 1988. "Towards a Definition of Nominal Specifiers in Amharic", Proceedings of the Eighth International Conference of Ethiopian Studies. Institute of Ethiopian studies, Addis Ababa University, (599-613).

Bender, Marvin, Leonel. 1969. "Two problems in Amharic Phonetics-the Sixth order Vowel and the Verb suffixes", Journal of Ethiopian studies. 7.2, Addis Ababa University.

________, Cowley R., Ferguson C.A., Hailu Fulas, Getachew Haile.1976. "The Amharic Language"; Language in Ethiopia. London: Oxford University press.(77-97).

________ et al. 1976. Language in Ethiopia. London: Oxford University press.

Brown, H.D. 1980. Principles of Language Learning And Teaching. England Cliffs, N.J.: Prentice Hall.

Brown F.G. 1983. Principles of Education and Psychological Testing. England Cliffs, N.J.: Prentice Hall.

Carol,M.Eastman. 1978. Linguistic Theory And Language Description.

Cowley Rager. 1967. "The Standardization of Amharic Spelling",Journal of Ethiopian Studies. 5:2 (1-18).

_______ .1969. "A and b Verb stem types in Amharic": Journal of Ethiopian Studies. 7, (1-13).

Dawkins, C.H. 1960. The Fundamentals of Amharic. Addis Ababa: Sudan Interior Mission.

Dejenie Leta Gebeyehou.1990."Achievement,Washback, And Proficiency in School Learning Examination:A Case of Innovation in An Ethiopian Setting".(PhD. Thesis).

Ellis, R. 1985. Understanding Second Language Acuisition. Oxford: University Press.

Hailu Fulas. 1964."Derived Nominal Patterns in Amharic", Ph.D. Thesis, UCLA.

_______ 1969. "Notes on the verbal Noun and Possession Markers", Journal of Ethiopian Studies.

Hatch, E. and Farhady, H. 1982. Research Design and statistics Applied Linguistic. Rowley,Moss.: Newbury House.

Kapeliuk, Olga. 1984. "Semantic Analysis of some Morphological phenomena in Amharic", Proceddings of the Eighth International Confernence of Ethiopian Studies. Intstitute of Ethiopian Studies, (697-703).

Langacker, Ronald, W. 1973. Language and its structure: Some Fundamental linquistic concepts. Havourt Press; Jouanorice.

McArthur, Tom. 1990. A foundation coures for language Teachers. Combredge.

Mullen, D.S. 1986."Issues in the Morphology and phonology of Amharic: The Lexical Generation pronominal Clitics", Ph.D. Thesis. University of Ottaiva.

Podolsky, B. 1977. "Morphology of Amharic Verb"; Proceedings of the Fifth International Conference of Ethiopian Studies. Nice (91-96).

___ ________.1982. "Some problems in phonology and Morphology of Amharic"; Proceedings of the Seventh International Conference of Ethiopian Studies. Lund. (17-18).

Richards,J.C. and T.S.Rodgers. 1986. Apprcaches and Methods to Language Teaching: A description and Analysis. Combridge: Cambridge University Press.

Seligar, Hebert, W., and Shohamy, E. 1989. Second Language Research Methods. Oxford: Oxford University press.

Stern, H.H. 1983. Fundamental concepts of Language Teaching. Oxford: Oxford University press.

Spolsky, B 1989. Conditions for second Language Learning. Oxford: Oxford University press.

Taddele Addamu. 1990. Individual Differences In Second Language Learning In Formal Context. PhD. Thesis.

Taddese Beyene. 1988. "The pronouns in Amharic: a Re-examination of Their Morphology", Proceedings of the Ninth International Conference of Ethiopian Studies. Moscow, (120-130).

አባሪ 1 ለተማሪዎች የተሰጡ ስድስት ተከታታይ (3 ቅደመና 3 ድኅረ) ፈተናዎች

ማሰሰቢያ

ፈተና 1

ይህ ሙከራ /ቴስት/ ያማርኛ ቋንቋ ትምህርት አሰጣጥን ለማሻሻል ከሚደረጉ ጥናትና ምርምሮች ለንዱ የተዘጋጀ ነው። ጥናቱ ውጤታማ ይሆን ዘንድ ሙከራውን የምትሰሩ የ10ኛ ክፍል ተማሪዎች የምታውቁትን በትክክል መመለስ የማታውቁትን አናውቅም ማለት ይጠበቅባችኋል። የምታጡት ወይም የምታገኙት ምንም ማርክ የለም። ስማችሁን መፃፍም አያስፈልጋችሁም። የክፍል ቁጥራችሁን ግን ትጽፋላችሁ።

ቀን ________________፣

1 1 1 ሰዓት ________________፣

ጾታ ______ እድሜ ______ ክፍል ______ ቁጥር ______፤

ትዕዛዝ፤ ትክክለኛ ነው ብለህ የምታምንበትን መልስ በተሰጠህ ባዶ ቦታ ላይ በመጻፍ ከ1-10 ላሉት ጥያቄዎች መልስ ስጥ። ጊዜ 15 ደቂቃ

1. "ሄደ" ብሎ "ሄዱ" ሲል የተጨመረው
ቅጥያ ______________ ነው።

2. "ጻፍ" ብሎ "ጻፊ" ሲል ሴቴ ጾታ የሚያመለክተው
ቅጥያ __________ ነው።

3. "እሱ" ብሎ "እነሱ" ሲል ብዛት ለማመልከት የተጨመረው
ቅጥያ______________ ነው።

4. "ከብቶች" በሚለው ቃል ውስጥ የብዙ ቁጥር አመልካቹ
ቅጥያ ______________ ነው።

5. "ልጅ" ብሎ "ልጆች" ሲል ብዛት አመልካቹ
ቅጥያ ______________ ነው።

6. ልጅ ብሎ ልጂት ሲል እሷ የሚል ሃሣብ በመስጠት
ሴቴ ጾታ የሚያመለክተው ቅጥያ __________ ነው።

7. "ሙት" ብሎ "ሙታን" ሲል ብዛት ለሚመለከት የተጨ
መረው ቅጥያ______________ ነው።

8. "ጠራች" በሚለው ቃል ውስጥ ባለቤት አመልካቹ ማለትም
"እሷ" የሚል ፍቺ የሚሰጠን ቅጥያ__________ ነው።

9. "ሂድ" ለወንድ ሲሆን "ሂጂ" ለሴት ነው።
"ሂጂ" በሚለው ቃል ውስጥ ሴቴ ጾታ አመልካቹ

ቅጥያ ________________ ነው።

10. "መታችሽ" በሚለው ቃል ውስጥ ተሣቢ አመልካቹ ማለትም "አንቺን" የሚል ፍቺ የሚሰጠን ቅጥያ ________________ ነው።

<u>በአራሚዎች ብቻ የሚሞላ</u>

ትክክል ከ10_____ በመቶኛ_______ ፤

ስህተት ከ10_____ በመቶኛ_______ ፤

ፈተና 2

ማሰሰቢያ

ይህ ሙከራ /ቴስት/ ያማርኛ ቋንቋ ትምህርት አሰጣጥን ለማሻሻል ከሚደረጉ ጥናትና ምርምሮች ለንዱ የተዘጋጀ ነው። ጥናቱ ውጤታማ ይሆን ዘንድ ሙከራውን የምትሰሩ የ10ኛ ክፍል ተማሪዎች የምታውቁትን በትክክል መመለስ የማታውቁትን አናውቅም ማለት ይጠበቅባችኋል። የምታጡት ወይም የምታገኙት ምንም ማርክ የለም። ስማችሁን መፃፍም አያስፈልጋችሁም። የክፍል ቁጥራችሁን ግን ትጽፋላችሁ።

ቀን ___________፤

ክድ___________፤

2 2 2

ፆታ ______ እድሜ ______ ክፍል ______ ቁጥር ______፤

ያፍ መፍቻ ቋንቋህ ሽ ____________፤

ትዕዛዝ፤ ትክክለኛ ነው ብለህ የምታምንበትን መልስ በተሰጠህ ባዶ ቦታ ላይ በመጻፍ ከ1-10 ላሉት ጥያቄዎች መልስ ስጥ። ጊዜ 15 ደቂቃ

1 "ደብተር" ብሎ "ደብተሮች" ሲል ብዛት

አመልካች ቅጥያ ________________ ነው።

2. "ተራራዎች" በሚለው ቃል ውስጥ የብዙ ቁጥር አመልካች ቅጥያ ________________ ነው።

3. "ከራ" ብሎ "ከሩ" ሲል ብዛት ለማመልከት የተጨመረው ቅጥያ ________________ ነው።

4. "ጻድቅ" ብሎ "ጻድቃን" ሲል ብዛት ለማመልከት የተጨመረው ቅጥያ ________________ ነው።

5. "ቆቅ" ብሎ "ቆቂት" ሲል "እሷ" የሚል ሃሣብ በመስጠት ሴት ጾታ የሚያመለክተው ቅጥያ ________ ነው።

6. "እሱ" ብሎ "እነሱ" ሲል ብዛት ለማመልከት የተጨመረው ቅጥያ ________________ ነው።

7. "መጣች" በሚለው ቃል ውሰጠ ባለቤት አመልካች ማለትም "እሷ" የሚል ፍቺ የሚሰጠን ቅጥያ ____________ ነው።

8. "ሰጠችሽ" በሚለው ቃል ውስጥ ተሣቢ አመልካች ማለትም "ለአንቺ" የሚል ፍቺ የሚሰጠን ቅጥያ ______________ ነው።

9. "ሰብር" ብሎ "ሰበሪ" ሲል ሴቴ ጾታ የሚያመለክተው ቅጥያ ________________ ነው።

10. "ልበስ" ለወንድ ሲሆን "ለበሺ" ለሴት ነው።
"ልበሺ" በሚለው ቃል ውስጥ ሴቴ ጾታ አመልካች
ቅጥያ __________________ ነው።

<u>በአራሚዎች ብቻ የሚሞላ</u>

ትክክል ከ10______በመቶኛ______፣
ስህተት ከ10______በመቶኛ______፣

ፈተና 3

ማስሰቢያ

ይህ ሙከራ /ቴስት/ ያማርኛ ቋንቋ ትምህርት አሰጣጥን ለማሻሻል ከሚደረጉ ጥናትና ምርምሮች ለንዱ የተዘጋጀ ነው። ጥናቱ ውጤታማ ይሆን ዘንድ ሙከራውን የምትሰሩ የ10ኛ ክፍል ተማሪዎች የምታውቁትን በትክክል መመለስ የማታውቁትን አናውቅም ማለት ይጠበቅባችኋል። የምታጡት ወይም የምታገኙት ምንም ማርክ የለም። ስማችሁን መፃፍም አያስፈልጋችሁም። የክፍል ቁጥራችሁን ግን ትጽፉለችሁ።

ቀን____________፣

3 3 3 ክድ __________፣

ጾታ_______ እድሜ______ ክፍል_____ ቁጥር_____፤

ያፍ መፍቻ ቋንቋህ /ሽ/ ____________፤

ትዕዛዝ፤ ትክክለኛ ነው ብለህ የምታምንበትን መልስ በተሰጠህ በደ ቦታ ላይ በመጻፍ ከ1-10 ለሉት ጥያቄዎች መልስ ስጥ። ጊዜ 15 ደቂቃ

ተማሪዎች በሚለው ቃል ውስጥ የብዙ ቁጥር አመልከቹ ቅጥያ______________ ነው።

2. "እርሳስ" ብሎ "እርሳሶች" ሲል ብዛት አመልካች ቅጥያ ______________ ነው።

3. "ልዑል" ብሎ "ልዑላን" ሲል ብዛት ለማመልከት የተጨመረው ቅጥያ ___________ ነው።

4. "ተማሪ" ብሎ "ተማሩ" ሲል ብዛት ለሚመለከት የተጨመረው ቅጥያ ______________ ነው።

5. "እሱ" ብሎ "እነሱ" ሲል ብዛት ለማመልከት የገባው ቅጥያ ______________ ነው።

6. "ጎበዝ" ብሎ "ጎበዚት" ሲል እሷ የሚል ሃሣብ በመስጠት ሴቴ ጾታ የሚያመክተለው ቅጥያ ___________ ነው።

7. "ተናገር" ብሎ "ተናገሪ" ሲል ሴቴ ጾታ የሚያመለክተው ቅጥያ ______________ ነው።

8. "በርታ" ለወንድ ሲሆን "በርቺ" ለሴት ነው።
"በርቺ" በሚለው ቃል ውስጥ ሴቴ ጾታ አመለካቹ ቅጥያ ______________ ነው።

9. "ገበኝ" በሚለው ቃል ውስጥ ባለቤት አመልካቹ ማለት "እሷ" የሚል ፍቺ የሚሰጠን ቅጥያ ___________ ነው።

፡፡ "ገፋችሽ" በሚለው ቃል ውስጥ ተሣቢ አመልካቹ ማለትም "አንቺን" የሚል ፍቺ የሚሰጠን ቅጥ__________ነው።

<u>በአራሚዎች ብቻ የሚሞላ</u>

ሀ. ትክክል በመቶኛ----------

ለ. ስህተት በመቶኛ----------

ፈተና 4

ማሰሰቢያ፣

ይህ ሙከራ /ቴስት/ ያማርኛ ቋንቋ ትምህርት አሰጣጥን ለማሻሻል ከሚደረጉ ጥናትና ምርምሮች ሰንዱ የተዘጋጀ ነው። ጥናቱ ውጤታማ ይሆን ዘንድ ሙከራውን የምትሰሩ የ10ኛ ክፍል ተማሪዎች የምታውቁትን በትክክል መመለስ የማታውቁትን አናውቅም ማለት ይጠበቅባችኋል። የምታጡት ወይም የምታገኙት ምንም ማርክ የለም። ስማችሁን መፃፍም አያስፈልጋችሁም። የክፍል ቁጥራችሁን ግን ትጽፋለችሁ።

4 4 4

ከድ.----------------

ቀን ----------------

ፆታ______እድሜ _____ክፍል____ቁጥር-----

ያፍ መፍቻ ቋንቋህ/ሽ-------------------------

ትዕዛዝ፤ ትክክለኛ ነው ብለህ የምታምንበትን መልስ በተሰጠህ ባዶ ቦታ ላይ በመጻፍ ከ1-10 ላሉት ጥያቄዎች መልስ ስጥ። ጊዜ 10 ደቂቃ።

1 "ተማከረ" ብሎ "ተማከሩ" ሲል ብዛት ለማመልከት የተጨመረው ቅጥያ __________ ነው።

2 "አትስጥ" ለወንድ ሲሆን "አትስጪ" ለሴት ነው።

"አትስጪ" በሚለው ቃል ውስጥ ሴቴ ጾታ አመልካቹ ቅጥያ __________ ነው።

3. "ቅምጥል" ብሎ "ቅምጥሊት" ሲል ሴቴ ጾታ የሚያመለክተው ቅጥያ __________ ነው።

4. "ተጠያቂዎች" በሚለው ቃል ውስጥ የብዙ ቁጥር አመልካቹ ቅጥያ __________ ነው።

5. "ካህን" ብሎ "ካህናት" ቢል ብዛት ለማመልከት የተጨመረው ቅጥያ __________ ነው።

6. "ገደለች" በሚለው ቃል ውስጥ ባለቤት አመልካቹ ማለትም "እሷ" የሚል ፍቺ የሚሰጠን ቅጥያ ______ ነው።

7. "አመነችሽ" በሚለው ቃል ውስጥ ተሣቢ አመልካቹ ማለትም "አንቺን" የሚል ፍቺ የሚሰጠን ቅጥያ ______ ነው።

8. "ብርቱካን" ብሎ "ብርቱካኖች" ሲል ብዛት አመልካች ቅጥያ __________ ነው።

9. "አንተ" ብሎ "እናንተ" ሲል ብዛት ለማመልከት የገባው ቅጥያ __________ ነው።

10. "ተቆጣጠር" ለወንድ ሲሆን "ተቆጣጠሪ" ለሴት ነው፤ በሁለተኛው ቃል ውስጥ ሴቴ ጾታ የሚያመለክተው ቅጥያ

ነው ።

<u>በአራሚዎች ብቻ የሚሞላ</u>

ሀ. ትክክል በመቶኛ----------

ለ. ስህተት በመቶኛ----------

## ፈተና 5

### ማሳሰቢያ

ይህ ሙከራ /ቴስት/ያማርኛ ቋንቋ ትምህርት አሰጣጥን ለማሻሻል ከሚደረጉት ጥናትና ምርምሮች ለአንዱ የተዘጋጀ ነው። ጥናቱ ውጤታማ ይሆን ዘንድ ሙከራውን የምትሰሩ የ10ኛ ክፍል ተማሪዎች የምታውቁትን በትክክል መመለስ የማታውቁትን አናውቅም ማለት ይጠበቅባችኋል። የምታጡት ወይም የምታገኙት ምንም ማርክ የለም። ስማችሁን መጻፍም አያስፈልጋችሁም። የክፍል ቁጥራችሁን ግን ትጽፋላችሁ።

5 5 5

ከድ ..................

ቀን ..................

ጾት ________ እድሜ ክፍል________ቁጥር______፤

ያፍ መፍቻ ቋንቋህ ሽ ______፤

ትዕዛዝ፤ ትክክለኛ ነው ብለህ የምታመንበትን መልስ በተሰጠህ ባዶ ቦታ ላይ በመጻፍ ከ1-10 ላሉት ጥያቄዎች መልስ ስጥ። ጊዜ 10 ደቂቃ።

1. "አንተ" ብሎ "አናንተ" ሲል ብዛት ለማመልከት የገባው ቅጥያ________ ነው።

2. "አስተባበረ" ብሎ "አስተባበሩ" ሲል ብዛት ለማመልከት የተጨመረው ቅጥያ _______ ነው።

3. "ግድርድር" ብሎ "ግድርድሪት" ሲል "እሷ" የሚል ሃሣብ በመስጠት ሴቴ ጾታ የሚያመለክተው ቅጥያ _______ ነው።

4. "መስተዋድድ" ብሎ "መስተዋድዶች" ሲል ብዛት አመልካቹ ቅጥያ_______ ነው።

5. "ተጠባባቂዎች" በሚለው ቃል ውስጥ የብዙ ቁጥር አመልካቹ ቅጥያ_______ ነው።

6. "ነቢይ" ብሎ "ነቢያት" ቢል ብዛት ለማመልከት የጨመረው ቅጥያ _______ ነው።

7. "ገመገመች" በሚለው ቃል ውስጥ ባለቤት አመልካቹ

ማለትም እሷ የሚል ፍቺ የሚሰጠን ቅጥያ_____ ነው።

8. "ጠረጠረችሽ" በሚለው ቃል ውስጥ ተሣቢ አመልካቹ ማለትም እንቺን" የሚል ፍቺ የሚሰጠን ቅጥያ _____ ነው።

9. "አስጠንቅቅ" ብሎ "አስጠንቅቂ" ሲል ሴቴ ጾታ የሚያመለክተው ቅጥያ _______ ነው።

10. "አትውሰድ" ለወንድ ሲሆን "አትውሰጂ" ለሴት ነው።

አትውሰጂ፡ በሚሰው ቃል ውስጥ ሴቴ ጾታ አመልካቹ ቅጥያ _____ ነው።

<u>በአራሚዎች ብቻ የሚሞላ</u>

ሀ. ትክክል = በመቶኛ ..........

ለ. ስህተት = በመቶኛ ..........

ፈተና 6

ማሰሰቢያ

ይህ ሙከራ /ቴስት/ ያማርኛ ቋንቋ ትምህርት አሰጣጥን ለማሻሻል ከሚደረጉ ጥናትና ምርምሮች ሳንዱ የተዘጋጀ ነው። ጥናቱ ውጤታማ የሆን ዘንድ ሙከራውን የምትሰሩ የ10ኛ ክፍል ተማሪዎች የምታውቁትን በትክክል መመለስ የማታውቁትን አናውቅም አናውቅም ማለት ይጠበቅባችኋል። የምታጡት ወይም የምታገኙት ምንም ማርክ የለም። ስማችሁን መጻፍም አያስፈልጋችሁም። የክፍል ቁጥራችሁን ግን ትጽፋላችሁ።

6 6

ከድ ----------------

ቀን ----------------

ጾት_____እድሜ______ክፍል_____ቁጥር____፤

ያፍ መፍቻ ቋንቋህ ሽ __________፤

ትዕዛዝ፤ ትክክለኛ ነው ብለህ የምታምንበትን መለስ በተሰሀ ባዶ ቦታ ላይ በመጻፍ ከ1-10 ላሉት ጥያቄዎች መልስ ስጥ። ጊዜ 10 ደቂቃ።

1 አደናቀፈች በሚለው ቃል ውስጥ ባለቤት አመልካቹ ማለትም "እሷ" የሚል ፍቺ የሚሰጠን ቅጥያ______ነው።

2 "አንተ" ብሎ "እናንተ" ሲል ብዛት ለማመለከት የገባው ቅጥያ ________ ነው።

3. "አ ስ ደ ስ ት" ለ ወ ን ድ ስ ሆ ን "አ ስ ደ ስ ቺ" ለ ሴ ት ነው።በሁለተኛው ቃል ውስጥ ሴቴ ጾታ አመልካቹ ቅጥያ ________ ነው።

4. "ተምነሽነሽ" ብሎ "ተምነሽነሺ" ሲል ሴቴ ጾታ የሚያ መለከተው ቅጥያ ________ ነው።

5. "መስተጻምሮች" ሲል ብዛት አመልካቹ ቅጥያ________ ነው።

6. "ቅልብልብ" ብሎ "ቅልብልቢት" ሲል "ኢቲ" የሚል ሃሣብ በመስጠት ሴቴ ጾታ የሚያመለክተው ቅጥያ ______ ነው።

7. ስለአስተናገዱ በሚለው ቃል ወስጥ ብዙ ቁጥር አመልከቹ ቅጥያ ______ ነው።

8. ሰማእት ብሎ ሰማእታት ቢል በሁለተኛው ቃል ውስጥ ብዙ ቁጥር አመልከቹ ቅጥያ ________ ነው።

9. "ማስገንዘቢያዎች" በሚለው ቃል ውስጥ የብዙ ቁጥር አመልካቹ ቅጥያ________ ነው።

10. "አስለፈለፈችን" በሚለው ቃል ውስጥ ተሣቢ አመልካቹ

ማለትም "አኛን" የሚል ፍቺ የሚሰጠን ቅጥያ ____ ነው።

<u>በአራሚዎች ብቻ የማሞሉ</u>

ሀ ትክክል በመቶኛ

ለ ስሀተት በመቶኛ

ሠንጠረዥ 2 ጥሬ ውጤት (Row Data)

| የተማሪ ኮድ | ፈ1 | ፈ2 | ፈ3 | X̄ | ፈ4 | ፈ5 | ፈ6 | X̄ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 114 | 2 | 2 | 2 | 2 | 8 | 10 | 10 | 9.33 |
| 223 | 2 | 2 | 2 | 2 | 7 | 8 | 7 | 7.33 |
| 323 | 3 | 2 | 2 | 2.33 | 8 | 10 | 10 | 9.33 |
| 414 | 2 | 2 | 2 | 2 | 3 | 2 | 3 | 2.67 |
| 524 | 2 | 2 | 2 | 2 | 8 | 8 | 8 | 8 |
| 613 | 4 | 5 | 4 | 4.33 | 10 | 10 | 10 | 10 |
| 724 | 2 | 2 | 2 | 2 | 8 | 7 | 7 | 7.33 |
| 824 | 1 | 2 | 3 | 2 | 7 | 8 | 8 | 7.67 |
| 923 | 4 | 1 | 3 | 2.67 | 10 | 8 | 9 | 9 |
| 1013 | 2 | 1 | 2 | 1.67 | 3 | 3 | 3 | 3 |
| 1113 | 2 | 3 | 2 | 2.33 | 9 | 9 | 9 | 9 |
| 1214 | 2 | 2 | 2 | 2 | 8 | 6 | 7 | 7 |
| 1323 | 2 | 2 | 2 | 2 | 6 | 6 | 6 | 6 |
| 1413 | 3 | 3 | 3 | 3 | 9 | 6 | 7 | 7.33 |
| 1513 | 2 | 2 | 3 | 2.33 | 8 | 8 | 8 | 8 |
| 1613 | 3 | 2 | 3 | 2.67 | 8 | 9 | 8 | 8.33 |
| 1714 | 3 | 2 | 3 | 2.67 | 10 | 10 | 10 | 10 |
| 1824 | 5 | 3 | 4 | 4 | 9 | 8 | 9 | 8.67 |
| 1923 | 2 | 3 | 3 | 2.67 | 8 | 8 | 8 | 8 |
| 2024 | 2 | 3 | 3 | 2.67 | 8 | 9 | 9 | 8.67 |
| 2113 | 2 | 2 | 2 | 2 | 9 | 10 | 10 | 9.67 |
| 2214 | – | 3 | 3 | 2 | 9 | 8 | 8 | 8.33 |
| 2313 | 5 | 5 | 5 | 5 | 10 | 8 | 9 | 9 |
| 2413 | 1 | 2 | 3 | 2 | 4 | 3 | 4 | 3.67 |
| 2623 | 2 | 2 | 2 | 2 | 10 | 10 | 10 | 10 |

የነጥብ ዝርዝር / ከ [illegible] /

4 = ገምርና ለቶ ያብራ ት

3 = ገምርና ለቶ የሬ ት

2 = ቢት

1 = [illegible]

ፈ = ፈተና

X̄ = አማካይ

| [illegible] | [illegible]1 | [illegible]2 | [illegible]3 | $\bar{X}$ | [illegible]4 | [illegible]5 | [illegible]6 | $\bar{X}$ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 2723 | 2 | 2 | 2 | 2 | 7 | 10 | 10 | 9 |
| 2823 | 2 | 4 | 4 | 3.33 | 10 | 10 | 10 | 10 |
| 2913 | 2 | 2 | 2 | 2 | 9 | 10 | 10 | 9.67 |
| 3123 | 1 | 3 | 2 | 2 | 4 | 4 | 4 | 4. |
| 3223 | 2 | 3 | 3 | 2.67 | 5 | 7 | 8 | 6.67 |
| *3323 | – | 2 | 2 | 1.33 | 4 | 4 | 4 | 4 |
| 3523 | 1 | 2 | 2 | 1.67 | 6 | 7 | 7 | 6.67 |
| 3623 | 3 | 3 | 3 | 3 | 10 | 9 | 8 | 9 |
| 3724 | 2 | 2 | 2 | 2 | 7 | 6 | 6 | 6.33 |
| 3813 | 2 | 2 | 2 | 2 | 9 | 9 | 9 | 9 |
| 3913 | 1 | 1 | 1 | 1 | 8 | 8 | 8 | 8 |
| 4023 | 4 | 4 | 4 | 4 | 10 | 10 | 10 | 10 |
| *4123 | 3 | 2 | 2 | 2.67 | 4 | 3 | 3 | 3.33 |
| 4224 | 2 | 2 | 2 | 2 | 9 | 9 | 9 | 9 |
| *4324 | – | 2 | 3 | 1.67 | 4 | 4 | 4 | 4 |
| 4413 | 3 | 2 | 3 | 2.67 | 7 | 9 | 8 | 8 |
| 4523 | 1 | 3 | 3 | 2.33 | 8 | 10 | 10 | 9.33 |
| 4613 | 2 | 2 | 2 | 2 | 8 | 9 | 7 | 8 |
| 4723 | 2 | 2 | 2 | 2 | 7 | 10 | 8 | 8.33 |
| *4813 | 2 | 2 | 2 | 2 | 2 | 2 | 2 | 2 |
| 4913 | 2 | 3 | 4 | 3 | 8 | 8 | 8 | 8 |
| 5013 | 2 | 2 | 3 | 2.33 | 8 | 5 | 7 | 6.67 |
| '5113 | 5 | 5 | 5 | 5 | 10 | 10 | 10 | 10 |
| 5214 | 4 | 4 | 4 | 4 | 10 | 10 | 10 | 10 |
| 5323 | 3 | 3 | 3 | 3 | 9 | 7 | 7 | 7.67 |

| የተማሪው ኮድ | ፈ1 | ፈ2 | ፈ3 | $\bar{X}_1$ | ፈ4 | ፈ5 | ፈ6 | $\bar{X}_2$ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 5413 | 4 | 4 | 5 | 4.33 | 10 | 10 | 10 | 10 |
| *5523 | 1 | 1 | 1 | 1 | 3 | 3 | 3 | 3 |
| 5623 | 2 | 3 | 3 | 2.67 | 7 | 6 | 7 | 6.67 |
| 5713 | 2 | 3 | 3 | 2.67 | 8 | 8 | 8 | 8 |
| 5824 | 1 | 2 | 2 | 1.67 | 7 | 5 | 5 | 5.67 |
| 5923 | 2 | 2 | 3 | 2.33 | 8 | 10 | 9 | 9 |
| 6023 | 2 | 2 | 2 | 2 | 3 | 4 | 4 | 3.67 |
| *6123 | 2 | 2 | 2 | 2 | 3 | 3 | 3 | 3 |
| 6223 | 1 | 3 | 3 | 2.33 | 5 | 8 | 7 | 6.67 |
| 6313 | 2 | 3 | 3 | 2.67 | 8 | 9 | 10 | 9 |
| 6423 | 1 | 1 | 1 | 1 | 7 | 8 | 7 | 7.33 |
| 6523 | 1 | 2 | 2 | 1.67 | 6 | 7 | 8 | 7 |
| 6613 | 3 | 3 | 3 | 3 | 8 | 8 | 8 | 8 |
| 6713 | 5 | 4 | 3 | 4 | 10 | 9 | 10 | 9.67 |
| *6823 | 2 | 2 | 2 | 2 | 2 | 2 | 2 | 2 |
| 6923 | 4 | 3 | 2 | 3 | 10 | 10 | 10 | 10 |
| *7023 | 1 | 2 | 2 | 1.67 | 4 | 3 | 3 | 3.33 |
| 7113 | 2 | 2 | 2 | 2 | 8 | 9 | 9 | 8.67 |
| 7224 | 2 | 2 | 2 | 2 | 9 | 10 | 10 | 9.67 |
| 7314 | 2 | 2 | 2 | 2 | 8 | 9 | 7 | 8 |
| 7413 | 1 | 2 | 2 | 1.67 | 3 | 4 | 4 | 7.33 |
| 7523 | 1 | 1 | 1 | 1 | 6 | 8 | 9 | 7.67 |
| 7613 | 2 | 2 | 2 | 2 | 9 | 10 | 10 | 9.67 |
| ድምር | 159 | 177 | 187 | 174.69 | 532 | 545 | 545 | 545.0 |

አባሪ 3 Summations obtained from the data collected

$\Sigma T$

$\Sigma T_1 = 159$
$\Sigma T_2 = 177$
$\Sigma T_3 = 187$
$\Sigma \bar{X}_1 = 174.69$

$\Sigma T_4 = 532$
$\Sigma T_5 = 545$
$\Sigma T_6 = 547$
$\Sigma \bar{X}_2 = 545.02$

$\Sigma T^2$

$\Sigma T_1^2 = 450$
$\Sigma T_2^2 = 487$
$\Sigma T_3^2 = 527$
$\Sigma \bar{X}_1^2 = 470.73$

$\Sigma T_4^2 = 4283$
$\Sigma T_5^2 = 4588$
$\Sigma T_6^2 = 4526$
$\Sigma \bar{X}_2^2 = 4933.36$

$\Sigma (T \times T)$

$\Sigma (T_1 \times T_2) = 432$
$\Sigma (T_2 \times T_3) = 494$
$\Sigma (T_1 \times T_3) = 450$

$\Sigma (T_4 \times T_5) = 4344$
$\Sigma (T_5 \times T_6) = 4471$
$\Sigma (T_4 \times T_6) = 4324$

$\Sigma D$

$\Sigma D_1 \ (T_4 - T_1) = 373$
$\Sigma D_1^2 \ (T_4 - T_1)^2 = 2190$
$\Sigma D_2 \ (T_5 - T_2) = 374$
$\Sigma D_2^2 \ (T_5 - T_2)^2 = 2276$
$\Sigma D_3 \ (T_6 - T_3) = 364$
$\Sigma D_3^2 \ (T_6 - T_3) = 2186$

$\Sigma D_t \ (\bar{X}_2 - \bar{X}_1)^2 = 361.02$
$\Sigma D_t^2 (\bar{X}_2 - \bar{X}_1)^2 = 2099.82$

አበሪ 4

# ማረጋገጫ

እኔ አብርሃም ጎዝጉዜ ግዛው፣ "ያማርኛ መደብ፣ ጸትና ቁጥር አመልካች ቅጥያ ምዕላደችን ማስተማሪያ አንድ ስልት" በሚል ርዕስ ባቀረብኩት በዚህ ጥናታዊ ጽሑፍ ውስጥ የሌሎች ባለሙያዎችን ሃሳቦች ተገቢውን የባለቤትነት መብት ጠብቄ ከመጥቀሴ በስተቀር ሥራው በወጥነት የራሴ መሆኑን በፊርማዬ አረጋግጣለሁ።

አብርሃም ጎዝጉዜ